ዲላ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረምረቃ ትምህርት ቤት

የአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ፅሑፍ ትምህርት ክፍል

# የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎችአቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ

(የአርት ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)

በላዋይሽ አየልኝ

ነሐሴ 2012 ዓ.ም

ዲላ

ዲላ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረምረቃ ትምህርት ቤት

የአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ፅሑፍ ትምህርት ክፍል

# የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትየሰዋስው ትምህርት መልመጃዎችአቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ

በላዋይሽ አየልኝ

አማርኛን በማስተማር የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ነጥቦች በከፊል ለማሟላት ለአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ፅሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ

የጥናቱ አማካሪ፡-

ዶ/ር ኢዮብ ቀለመወርቅ

ነሐሴ 2012 ዓ.ም

ዲላ

**ዲላ ዩኒቨርሲቲ**

**የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት**

**የአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርትክፍል**

እኛ ከዚህ በታች የፈረምነው በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ በሚል ርዕሥ፣ በላዋይሽ አየልኝ ተዘጋጅቶ አማርኛን በማስተማር ለአርት ማስተርስ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበው ይህ ጥናት፣ ከዩኒቨርሲቲው ደንብ ጋር የሚጣጣምና የአዲስነትና ጥራት ደረጃን የሚያሟላ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

**የፈተና ቦርድ አባላት**

የቦርድ ሰብሳቢ ____________________ ፊርማና ቀን __________

የውጭ ፈታኝ ____________________ ፊርማና ቀን __________

የውስጥ ፈታኝ ____________________ ፊርማና ቀን __________

አማካሪ ____________________ ፊርማና ቀን __________

# ማረጋገጫ

“በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ” በሚል ርዕሥ በዲላ ዩኒቨርሲቲ፣ የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ፅሑፍ ትምህርት ክፍል፣ **አማርኛ ቋንቋን በማስተማር** ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረብኩት ይህ ጥናት፣ ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ ወጥ የራሴ ሥራ መሆኑን፣ የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

**ላዋይሽ አየልኝ**

____________

**ነሐሴ 2012 ዓ.ም**

# ምሥጋና

በመጀመሪያ ደረጃ ይህ ጥናት ተጀምሮ እስከሚያልቅ ድረስ በሙሉ ጤንነት የተለያዩ ተግባራትን ከቦታ ቦታ እየተዘዋወርኩ እንዳከናውን ላደረገኝ ለእመቤታችን ለድንግል ማሪያም ልጅ ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምሥጋና ይገበዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ላይ ጥናቱ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በአካልም ሆነ በስልክ እንዲሁም በኢ-ሜል የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ጥናቱን አሁን ባለበት ደረጃ እንዲደርስ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ አስተዋፅኦ ያበረከቱልኝ ዶ/ር ኢዮብ ቀለመወርቅ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

በስተመጨረሻም ከጎኔ በመሆን በሀሳብም ሆነ የተለያዩ ድጋፎችን በማበርከት ለጥናቱ መሳካት ከፍተኛ የሆነ ጥረት ስታደርግልኝ ለነበረችው እናቴ ጥሩአየሁ አበበ እና ለጓደኞቼ በሙሉ የከበረ ምሥጋናዬን ከልብ አቀርባለሁ፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምሥጋና ............ i

ማውጫ............ ii

አጠቃሎ ............ iv

ምዕራፍ አንድ፡-መግቢያ............ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ............ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ............ 3

1.3 የጥናቱ ዓላማ ............ 3

1.4 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ............ 4

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ............ 4

1.6 የጥናቱ ወሰን ............ 4

ምዕራፍ ሁለት፡- የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ............ 5

2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ክለሳ............ 5

2.1.1 የሰዋስው ምንነት............ 5

2.1.2 የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ............ 6

2.1.2.1 የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ በጥንታዊ መማሪያ መጻሕፍት............ 6

2.1.2.2 የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ በዘመናዊ የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት............ 6

2.1.2.2.1 የቋንቋውን ሥርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት አቀናጅቶ ከማቅረብ አንፃር ............ 7

2.1.2.2.2 ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚሰጥ የሰዋስው መልመጃ አቀራረብ ............ 7

2.1.2.2.3 ሂደት ተኮርን መሠረት በማድረግ የሚዘጋጅ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ አቀራረብ ............ 8

2.1.2.2.4 እውናዊነትን የተላበሰ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ አቀራረብ............ 9

2.1.3 በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀት............ 9

2.1.3.1 ተከታታይነት............ 10

2.1.3.2 ተለጣጣቂነት ............ 11

2.1.3.3 ውህደት ............ 11

2.1.4 የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ምንነት ............ 12

2.1.5 የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያለው ግንኙነት ............ 13

2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ..... 14

ምዕራፍ ሶስት፡-የጥናቱ ንድፍና ዘዴ ..... 16

3.1 የጥናቱ ንድፍ ..... 16

3.2 የናሙና አመራረጥ ስልት ..... 16

3.3 የመረጃ መሰብሰያ ስልት ..... 17

3.4 የመረጃመተንተኛስልት ..... 17

ምዕራፍ አራት፡-የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ..... 18

4.1 የመረጃ ትንተና ..... 18

4.1.1 በዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው መልመጃዎች አቀራረብ ..... 20

4.1.1.1 በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት የቋንቋውን ስርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት አቀናጅቶ ከማቅረብ አንጻር ..... 20

4.1.1.2 በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍት የተማሪ ተኮር አቀራረብ ..... 25

4.1.1.3 በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት የሂደት ተኮር አቀራረብ ..... 28

4.1.1.4 በዘጠነኛና በአሥረኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍት ውስጥ እውናዊነት ተላብሶ ከማቅረብ አንጻር ..... 32

4.1.2 ዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀት ..... 35

4.1.2.1 የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀት ከተከታታይነት አንፃር ..... 35

4.1.2.2 የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀት ከተለጣጣቂነት አንፃር ..... 41

4.1.2.3 የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀት ከውህደት አንፃር ..... 48

4.1.3 የመማሪያ መጻህፍቱ ከመርሀ ትምህርቶቹ ጋር ያላቸው ዝምድና ..... 49

4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ..... 51

ምዕራፍ አምስት፡-ማጠቃለያ እና አስተያየት ..... 54

5.1 ማጠቃለያ ..... 54

5.2 አስተያየት ..... 56

ዋቢ. ፅሑፎች

አባሪዎች

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ መፈተሽ በመሆኑ ገላጭ ንድፍን የተከተለ ነው፡፡ አላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ለጥናቱ የመረጃ ምንጭ ሆነው ያገለገሉት በ2004 ዓ.ም ታትመው አሁን ሥራ ላይ በዋሉት የዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትና መርሃ-ትምህርቶቹ ናቸው፡፡ ከነዚህ የመረጃ ምንጮች በሰነድ ፍተሻ የተሰበሰቡት መረጃዎች አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልትን በመጠቀም ተተንትኗል፡፡ የጥናቱ ግኝትም በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ከአቀራረብ መገምገሚያ መስፈርቶች አንፃር አብዛኛዎቹ የሰዋስው መልመጃዎች የቋንቋውን ስርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት አቀናጅተው የማያቀርቡ፣ እውነታዊነትን ያልተላበሱ፣ ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የማይሰጡ፣ ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብን መሠረት በማድረግ ያልቀረቡ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ ከአደረጃጀት አንፃር የመገምገሚያ መስፈርቶች ደግሞ በመማሪያ መፅሐፍቱ ውስጥ ከቀጣይነት አንፃር ሲታይ በውስጡ ያካተቷቸው መልመጃዎች ሰፊና ቀጣይነት ባለው መልኩ የቀረቡ እንደሆኑ ተለይቷል፡፡ በተመሳሳይ ከተለጣጣቂነት አንፃር በመማሪያ መፅሐፍቱ ውስጥ ያሉት የሰዋስው መልመጃዎች በተወሰነ መልኩ ደረጃቸውን ጠብቀው የተደራጁ ቢሆንም፣ በተወሰነ መልኩ የመልመጃ ድግግሞሽ ላይ ችግር ተስተውሏል፡፡ በመጨረሻም ከውህደት አንፃር ስታዩ በሚፈለገው መልኩ ተደራጅተው የቀረቡ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ሌላው ደግሞ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች በሙሉ በመርሃ-ትምህርቱ ውስጥ ተካተው የተገኙ እና የመርሃ-ትምህርቱና የመማሪያ መጻሕፍቱ ተጣጥመው የቀረቡ መሆናቸውን ለማየት ተችሏል፡፡ በመጨረሻም የጥናቱን ግኝት መሰረት በማድረግ ከአቀራረብና ከአደረጃጀት አንፃር ሊከናወኑ የሚገባቸው የመፍትሔ ሃሳቦች ተጠቁመዋል፡፡

# ምዕራፍአንድ፡- መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ቋንቋ ማለት የሀሳብ ማስተላለፊያና የማንነት መግለጫ መሣሪያ በመሆኑ የሰው ልጅ በንግግርም ሆነ በፅሁፍ አማካኝነት የተሟላ ሀሳብን ለመሰሉ በትክክል ለማስተላለፍ ወይም ደግሞ ከሰዎች ጋር በትክክል ለመግባባት የቋንቋውን ስርዓት ከአጠቃቀሙ ማለትም ከተግባቦቱ ጋር አጣምሮ ማወቅ ያስፈልጋል (ባየ 2002፣xi)፡፡ ምክንያቱም ሰዋስው በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ከሚነሱ ነጥቦች ውስጥ አንዱና የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ብቃት ለማጎልበት የጀርባ አጥንት ስለሆነ ያለሰዋስው ውጤታማ በሆነ መንገድ በትክክል ለመግባባት አስቸጋሪ በመሆኑ ነው (Ellis 1997፡399)፡፡

ከምሁራን ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ቋንቋ ስርዓት ያለው በመሆኑ የሰው ልጅ በንግግርም ሆነ በፅህፈት ወቅት ሥርዓቱን ጠብቆ መልዕክቱን እንዲተላለፍ የሚያስችል እውቀት ያስፈልገዋል፡፡ ይህ እውቀት ደግሞ የሰዋስው እውቀት መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡

Krashen (1983:32) ሰዋስው በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ከሚነሱ ነጥቦች ውስጥ አንዱና የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ብቃት ለማጎልበት የጀርባ አጥንት ቢሆንም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን በቋንቋ ምሁራን ላይ ግን የተለያዩ ክርክሮች እንዳሉ የቋንቋ ምሁራን ያብራራሉ፡፡ የመጀመሪያው ክርክር የግብዓት መላምትን መሰረት በማድረግ የሚያብራሩ ሲሆን ዋናው ትኩረታቸውም በግብዓት ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ለተለያዩ ግብዓች የሚጋለጡ ከሆነ በቋንቋው በሚገባ እንዲግባቡና የቋንቋ ችሎታቸውንም እንዲያጎለብቱ ማድረግ ይቻላል የሚሉ ሲሆን ሁለተኛው ክርክር ደግሞ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ መደበኛ ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን እንዲለማመዱ የምናደርግ ከሆነ በቋንቋው በሚገባ መግባባት እንዲችሉ ማድረግ ይቻላል የሚሉ ናቸው፡፡ ሶስተኛው ክርክር ደግሞ ሰዋስውን በምናስተምርበት ጊዜ የተማሪዎችን እድሜና አዕምሮአዊ ብስለት ከግምት ውስጥ የምናስገባ ከሆነ ተማሪዎች በቋንቋው የመግባባት ክህሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ ይቻላል፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሀሳብ እንደምንረዳው ከሆነ ምንም እንኳን በሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ዙሪያ ላይ የተለያዩ አመለካከቶች ቢኖሩም የተማሪዎች ተግባቦታዊ ብቃት ለማጎልበት ቢዘጋጁም የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርትን ማካተት አስፈላጊ እንደሆነ

ነው፡፡ ምንክያቱም የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ መካተቱ ሀሳባቸውን፣ ስሜታቸውን ማለትም የተግባቦታዊ ብቃታቸውን እንዲያጎብቱ ለማድረግ የራሱ የሆነ አዎንታዊ አስተዋፆኦ ስላለው ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚቀርቡት የሰዋስው ተግባራት ስርዓቱ ላይ ብቻ ተንተርሰው ይቀርባሉ ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሰዋስዋዊ ህጉን ብቻ ለማስተማር ይልቅ ሰዋስውን ከእውነተኛ ዓለም ወይም ከሰዎች የዕለት ተዕለት የሕይወት ተሞክሮ ጋር እንዲሁም የቋንቋውን ስርዓት ከቋንቋው ፍቺና አገልግሎት ጋር በተቀናጀ መልኩ ማስተማር የተማሪዎችን ተግባታዊ ብቃት ማለትም የመናገር የማበብና የማዳመጥ በተለይ ደግሞ የመፃፍ ክህታቸውን ለማጎልበት ከፍተኛ የሆነ ሚና ስላለውና የሰዋስው ትምህርት ዋና ዓላማም ተማሪዎቹ ቋንቋውን በአግባቡ እንዲጠቀሙበት ከማስቻል ውጪ የሚታሰብ ስለማይሆን ነው (Harmer, 1991:46)::

ከሀሳቡ መረዳት እንደሚቻለው የሰዋስውን ትምህርት ተማሪዎች በሚማሩበት ጊዜ መዋቅርና ህግ ላይ ብቻ ትኩረት እንዳያደርጉ በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ያሉ መልመጃዎች የሰዋስው ትምህርት አቀራረብን ተከትለው ቢዘጋጁ የተማሪዎች ተግባቦታዊ ብቃት የሚዳብር መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ ጋር በተያያዘ Harmer (1991:257) እንደሚገልፁት ተገቢ በሆነ መልኩ የተዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ለተማሪዎቹ የቋንቋ ችሎታ መዳበር አስተዋጽዖ ያደርጋሉ፤ የትምህርቱን ይዘት በግልፅ ያመለክታሉ፤ ትምህርቱን ስኬታማ ለማድረግ የሚረዱ ተግባራትን ያሳያሉ፤ እንዲሁም ተማሪዎቹ የተለያየ ትኩረት መስጠት የሚኖርባቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ያመለክታሉ፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት በ2004 ዓ.ም ተሻሽለው በወጡት የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍትን በማየት በውስጡ የሚገኙ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ጥረት ይደረጋል፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ውስን ጥናቶች ቢኖሩም ከሌሎቹ ጥናቶች በተለየ ሁኔታ አለው ሊባል የሚችለው በ2010 ዓ.ም በሰላምና ተስፋዬ 1993 የታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት የሚያስችል ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡ ሰላም (2010) በተዘጋጀው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጸሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አመራረጥና አደረጃጀት ከሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው መርህ አንፃር በዚህ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ክፍተት እንዳለባቸውና ለክህሎት ትኩረት እንዳልሰጡ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ ሌላው በ1993 ዓ/ም በተስፋዬ

የተደረገው ጥናት በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፌ ፊት ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና ግምገማ በሚል ባጠኑት ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘት ያላቸው መልመጃዎች ለቋንቋው ፍቺ ትኩረት ያልሰጡና ከግብዓቶቹ ጥቅል ባህሪይ ወደ ዝርዝር ተደራጅተው የቀረቡ አለመሆናቸውን አሳይተዋል፡፡ በእነዚህ ጥናቶች እንደተመለከትነው በመማሪያ መጻሕፍት የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተፈትሸውና ጥናት ተደርጎባቸው ሊቀርቡ እንደሚገባ ነው፡፡ የዚህ ጥናት አቀራረብም በጥናቶቹ የተቀመጡትን የአቀራረብና የአደረጃጀት ክፍተቶች ታሳቢ በማድረግ ለማቅረብ የሞከረች ሲሆን ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች የሚለየው ተሻሽለው በወጡት የዘጠነኛና የአሥረኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑ ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

- ✓ አጥኝዋ በማስተማር ሂደት ተማሪዎች በተደጋጋሚ የሰዋስው ስህተቶችን ሲፈፅሙ በማስተዋሏ የእነዚህ ችግሮች ከመማሪያ መፅሐፍቱ ጋር የተያያዙ ይሆኑ እንደሁ በሚል መነሻ የመፅሐፍቱን አቀራረብና አደረጃጀት ለመመርመር ተነሳስታለች፡፡
- ✓ አጥኝዋ በማስተማር ቆይታዋ የሰዋስው መልመጃዎችን ስታሰራ ያስተዋለቻቸው ችግሮች መኖርና የሥራ ባልደረቦቿም የእነዚህን ዓይነት ችግሮችን እንዳስተዋሉ መስማቷ መፅሐፍቱን በደንብ መፈተሽ አነሳሽ ምክንያት ሆኗታል፡፡
- ✓ ሌላው ደግሞ ለሁለተኛ ዲግሪ መርሃ-ግብር እየተሰጠ ባለው የመርሃ ትምህርትና የመማሪያ መጻህፍት ዝግጅትና ግምገማ በሚለው ኮርስ ያገኘችው ዕውቀት የሰዋስው መልመጃዎችን መገምገምና ችግሮችን መርምሮ ማውጣት ፍላጎት ስላደረባት ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2004 ዓ.ም ተሻሽለው በተዘጋጁት የዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀትን መገምገም ሲሆን በውስጡ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች ይዟል፡፡

1 በዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ያላቸውን አቀራረብ መፈተሽ

2 በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀታቸው ምን እንደሚመስል መመርመር

3 መጻህፍቱ ከመርሃ ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ግንኙነት መፈተሽ

## 1.4 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ

በዚህ ጥናት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ይሞከራል፡፡

1. በዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ያላቸው አቀራረብ ምን ይመስላል?
2. በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀታቸው ምን ይመስላል?

3. መፅሐፍቱ ከመርሃ ትምህርቶቹ ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስላል?

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ለቋንቋ መማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች፣ ለቋንቋ መምህራን፣ ለተማሪዎች፣ ለተመራማሪዎች የሚከተሉት ጥቅሞች ይኖሩታል፡፡

1. ለቋንቋ መማሪያ መፅሀፍት አዘጋጅ ባለሙያዎች የሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት በመለየት እንዲያዘጋጁ ሊያግዝ ይችላል፡፡
2. የጥናቱን ውጤት መነሻ በማድረግ የመጻሕፍት አዘጋጆች ለክፍል ደረጃው ተስማሚ የሆኑ ስዋስዋዊ መልመጃዎችን ማዘጋጀት የሚያስችል ሀሳብ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡
3. የጥናቱን ውጤት መሠረት በማድረግ መምህራን ለተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎችን ለማስተማር ዕገዛ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በዋናነት ትኩረት አድርጎ የተነሳው በ2004 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር ታትመው በስራ ላይ የዋሉት የዘጠነኛና የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍትውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት መፈተሽ ላይ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡- የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

## 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ክለሳ

በዚህ ምዕራፍ በጥናቱ ርዕሠ ጉዳይ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሀሳቦች ከተለያዩ ድርሳናት ዳሰሳ በተገኙ እሳቤዎች መሠረት ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ አቀራረቡም ለጥናቱ በሚያመች መልኩ በንዑሳን ክፍሎች ተከፋፍሎ ሲሆን፤ ምዕራፉ ሁለት ዐበይት ክፍሎችን ይዟል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል የተለያዩ ትወራዊ እሳቤዎች የሚቀርቡበት ሲሆን፤ሁለተኛው ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የቀደምት ሥራዎች የሚቃኙበትና ከሚሠራው ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳስሎና ልዩነት የሚገለጽበት ነው፡፡

### 2.1.1 የሰዋስው ምንነት

ሰዋስው ማለት የአንድን የቋንቋ ሥርዓት ከድምፅ አሰካክእስከ ሐረግ አመሰራረቱ ድረስ ያለውን ሂደት የሚያሳይ ሳይንስ ነው በማለት (ባዬ2002፡xi)፡፡

Harmar (1991:1) በበኩሉ ቃላት ከአገባብ ጋር እራሳቸውን አስማምተው ትክክለኛ ዐረፍተ ነገር የሚመሠርቱበት ሥልት ነው፡፡ እራሳቸውን አስማምተው ሲል ከቁጥር፣ ከጊዜ፣ ከመደብ ወዘተ ሀሳብ እርስ በርስ የማይጋጩ የቋንቋውን አጠቃቀም ሥርዓት የሚጠብቁ መሆናቸውን ለመጠቆም ነው፡፡

ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ሰዋስው የአንድ ቋንቋ የአገባብ ሥርዓትን የሚያጠና ይህም ማለት የአገባብ ሥርዓትን ከድምፅ እስከ አረፍተ ነገር ያለውን የሚመለከት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

Brown (1994) ሰዋስው የአንድን ቋንቋ ከድምፅ ስርዓቱ ሀረግ ምሥረታ ሥርዓት ድረስ የሚያጠና ሥርዓቱ መሠረት የሚያደርገው ደግሞ የቋንቋውን ተናጋሪዎች ስምምነት ወይም ተናጋሪዎቹ የለመዱት በአጠቃቀም ወቅት ትክክል ወይም ስህተት በማለት የሚፈርዱትን ያጠቀለለ መሆኑን ጠቅሰው የሰዋስው ትኩረት በቋንቋ ቅርፅ ላይ ብቻ ሳይሆን በአጠቃቀሙ ላይ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

በአጠቃላይ የሰዋስውን ፅንሰ ሀሳብ በተመለከተ በርካታ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎችን የሚሰጡ ሲሆን ከላይ የተሰጡትን መነሻ ነጥቦች መሠረት በማድረግ በጥቅሉ ሰዋስው ቋንቋ መዋቅር

ወይም ሥርዓት ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ሲባል ሰዋስው የቃላትን ቅንጅት ሥርዓት የሚመከት በዐ.ነገር ደረጃ የሚታይ መሆኑን ነው፡፡

### 2.1.2 የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ

በታሪክ ደረጃ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ በመማርያ መጻሕፍት ውስጥ በዋናነት በሁለት መንገዶች እንደሚቀርብ የታሪክ ድርሳናት ያሳያሉ፡፡ የመጀመሪያው የመማሪያ መጻሕፍት የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ የመዋቅራውያንን ስልተ ትወራ አስተሳሰብ መሠረት አድርጎ የሚነሳ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የተግባቦታውያን ስልተ ትወራ አስተሳሰብን መሠረት አድርጎ የሚነሳ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ እነዚህ ስልተ ትወራዎች ጥንታውያን የሰዋስው ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴና ዘመናውያን የሰዋስው ትምህርት ማስተማርያ ዘዴ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ስለዚህ በእነዚህ ስልተ ትወራዎች የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች እንዴት ሊቀርቡ እንደሚችሉና አጠቃላይ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ያላቸው አመለካከት ወይም መርህ ምን እንደሆነ በዚህ ጥናት እንደሚከተለው ለማቅረብ ይሞከራል፡፡

#### 2.1.2.1 የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ በጥንታዊ መማሪያ መጻሕፍት

የሰዋስው መልመጃዎች የሚቀርቡበት ተማሪዎች የተለያዩ ሰዋስዋዊ ተግባራትን እንዲለማመዱ በማድረግ ነው፡፡ ይህ ሲባል በዚህ ስልተ ትወራ ተማሪዎች የቋንቋውን ሥርዓት መሠረት በማድረግ በመተካካትና በመለዋወጥ እንዲሁም ባዶ ቦታ በመሙላትና በምርጫ መልኩ እየደጋገሙ እንዲለማመዱ ያደርጋል (Tarone and Yule, 1989)፡፡ ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት ተማሪዎች እያንዳንዱን የቋንቋ ጡቦች ነጣጥለው የሚማሩ ከሆነ በታላሚው ቋንቋ የመግባባት እድላቸው ከፍተኛ ይሆናል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ (Richards and Rodgers, 2001)፡፡

ከሀሳቡ መረዳት እንደሚቻለው መዋቅራዊ ስልተ ትወራ ተማሪዎች በስዋስው ህግ ላይ ወይም መዋቅር ትኩረት እንደሚያደርጉ ያመለክታል፡፡

#### 2.1.2.2 የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ በዘመናዊ የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት

ተግባቦታዊ ስልት ትወራን መሠረት አድርጎ የሚዘጋጅ የቋንቋ መመሪያ መፃሕፍት ተማሪዎች የተለያ ምልክቶችን እንዴት መግለጽና መተንተን እንደሚችሉ የሚያሳዩና የሚያለማምዱ ሰዋስዋዊ ተግባራትን ማካተት ይኖርበታል (Richards and Rodgers, 2001)፡፡ አያይዘውምHarmer (1991)፣ እንደገለጹት ተግባራዊ ስልተ ትወራን መሠረት በማድረግ

የሚዘጋጅ የቋንቋ መማርያ መፃሕፍት ለቋንቋው አገልግሎት ወይም ፍቺ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች የቋንቋውን አገልግሎታዊ ተግባራትን መሠረት በማድረግ ይቀርባሉ፡፡ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች የቋንቋውን አገልግሎታዊ ተግባራትን መሠረት በማድረግ ይቀርባሉ፡፡ ለአውድ ትኩረት ይሰጣል፡፡ እውናዊነትን መሠረት ባደረጉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ላይ ያተኩራል፡፡ እንዲሁም በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት የሚቀርቡት ሰዋስዋዊ መልመጃዎች ወይም ተግባራት የተማሪዎችን የእርስ በርስ ግንኙነትን የሚያጠነክሩ፣ ተማሪዎች ያላቸውን ሃሳብ የሚለዋውጡበት ስሜታቸውን ለጓደኞቻቸው የሚገልጹበት፣ ተማሪዎች በቡድንና ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚያከናውኗቸውና የተማሪዎችን የመተማመን፣ የማደራጀትና የመግለጽ ብቃታቸውን የሚያጎለብቱ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 2.1.2.2.1 የቋንቋውን ሥርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት አቀናጅቶ ከማቅረብ አንፃር

የሰዋስው መልመጃ አቀራረብ ትርጉም ባለው አውድ ላይ ተመስርቶ የሚቀርፅ ከሆነ ውጤታማነቱ የጎላ ነው፡፡ ምክንያቱም ሰዋስው ከአውድ ውጪ የሚቀርብ ከሆነ ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ዐ.ነገሮችን ወደ ተለያዩ ክፍልፋዮች እየነጣጠሉ እንዲማሩ ከማድረግ ውጪ ተግባቦታዊ ብቃታቸውን ሊያጎለብቱበት ስለማይችሉ ነው፡፡ የሰዋስው መልመጃዎች አውድን መሠረት በማድረግ የሚቀርብ ከሆነ ግን ተማሪዎች የቋንቋውን ሥርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት አጣምረው እንዲማሩና እንዲጠቀሙ እንዲሁም ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ በእውኑ ህይወታቸው ውስጥ በመጠቀም ሀሳባቸውንና ስሜታቸውን ከመሰሎቻቸው ጋር እርስ በርስ እንዲግባቡና እንዲለዋወጡ የሚያደርጉ ናቸው(Nunan, 1989)፡፡

በአጠቃላይ አውድን መሠረት አድርገው የሚቀርቡ የሰዋስው መልመጃዎች ከትርጉምና ከአገልግሎት አንፃር ሲታዩ የዐ.ነገሩን ትክክለኛ ትርጉምና አገልግሎት ለይቶ ለማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም የቃላት ወይም የዐ.ነገር ትርጉም ወይም አገልግሎት ከአውድ ውጪ የተለየ ሲሆን አውድን መሠረት በማድረግ መቅረቡ እንደዚህ ዓይነቶችን ክፍተቶች ለመከላከልና የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት ለማጎልበት አስፈላጊ ስለሆነ ነው፡፡

### 2.1.2.2.2 ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚሰጥ የሰዋስው መልመጃ አቀራረብ

ተማሪ ተኮር አቀራረብ ማለት ተማሪዎች የመማር ማስተማሩ ሂደት ዋና ተዋናይ ሲሆኑ በጥንድና በቡድን በመሆን የተለያዩ ሰዋስዋዊ ተግባራትን እንዲያከናውኑ የሚደረግበት ስልት ነው፡፡ በዚህ ስልት ከመምህር ተግባር ይልቅ ለተማሪዎች ተግባር ከፍተኛ የሆነ ትኩረት

ይሰጣል።መምህሩ የመማር ማስተማሩን ሂደት ያመቻቻል እንዲሁም ይቆጣጠራል። የሰዋስው መልመጃዎች ደግሞ ከሥርዓቱ ይልቅ ተግባቦቱን መሠረት በማድረግ እንዲከናወኑ ያደርጋል።

በመሆኑም በቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው መልመጃዎች ተማሪ ተኮር አቀራረብን መሠረት በማድረግ ቢዘጋጁ ተመራጭነታቸው የጎላ ነው። ምክንያቱም ተማሪ ተኮር የሰዋስው መልመጃ አቀራረብ የተማሪዎችን የእርስ በርስ ግንኙነት የሚያጠነክር፣ የመተንተን፣ የማደራጀት፣ የመግለፅ ብቃታቸውንና የመማር ፍላጎታቸውን እንዲሁም ትብብራዊ መማርንና ተግባቦታዊ ብቃታቸውን የሚያዳብር፣ ተማሪዎች ያላቸውን ሀሳብ እንዲለዋውጡና ስሜታቸውን ለጓደኞቻቸው እንዲገልፁ የሚያደርግ ስልት ስለሆነ ነው (Cooper 1995 pp162-164)።

በአጠቃላይ ተማሪ ተኮር አቀራረብ ከቋንቋው ሥርዓት ይልቅ ለተግባቦቱ፣ ከመምህሩ ይልቅ ለተማሪው ከፍተኛ የሆነ ትኩረት ስለሚሰጥ የቋንቋውን ሥርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት አቀናጅቶ ለማስተማር አመቺ በመሆኑ በቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው መልመጃዎች ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚሰጡ የተማሪዎችን የእርስ በርስ ግንኙነትንና የመተንተን የማደራጀትና የማበልፀግ ብቃታቸውን የሚያጎለብት ስለሆነ ነው።

**2.1.2.2.3 ሂደት ተኮርን መሠረት በማድረግ የሚዘጋጅ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ አቀራረብ**

ሂደት ተኮርን የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ከምሳሌው ተነስቶ ወደ ህጉ ወይም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚቀርብ ስለሆነ ተማሪዎች ሰዋስውን በቀጥታ የሚማሩበት ሳይሆን ቋንቋቀወነወ በሚጠቀሙበት ጊዜ ከተሞክሯቸው ህጉን እንዲለዩ ወይም እንዲማሩበት የሚደረግበት ስልት ነው። በመሆኑም ሂደት ተኮር የሰዋስው አቀራረብን መሠረት በማድረግ የሚዘጋጁ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች የቋንቋውን ሥርዓት ፍቺና አገልግሎት አቀናጅቶ ለማስተማር አመቺ በመሆናቸው የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ብቃት ለማዳበር ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ አስተዋፅኦ አላቸው። ምክንያቱም ሂደት ተኮር የሰዋስው አቀራረብ ስልትን መሠረት በማድረግ የሚዘጋጁ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ለተማሪዎች ነፃነትን የሚሰጡና ተማሪዎች ትምህርቱን በንቃት እንዲማሩ የሚያደርጉ እንዲሁም የተማሪዎችን የችግር ፈቺነት ክህሎት የሚዳብሩና ትብብራዊ መማርን የሚጨምሩ ስለሆነ ነው (Brown, 1994)።

### 2.1.2.2.4 እውናዊነትን የተላበሰ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ አቀራረብ

የሰዋስው መልመጃዎች ይበልጥ ተግባራዊ ገፅታውን እንዲያጎለብቱ ከተፈለገ ተግባራቱ ወይም መልመጃዎች በመማርያ መፃሕፍት ውስጥ በሚቀርቡበት ጊዜእውነታዊነትን የተላበሱ ቢሆኑ ተመራጭ ነው፡፡ ምክንያቱም ለእውነተኛ ዓላማ እውናዊ የሆኑ ተግባራትን መጠቀም አስፈላጊ ስለሆነ ነው፡፡ እውናዊ የሆኑ የሰዋስው ተግባራት ሲባል በእውነተኛ ተግባቦት ውስጥ ሰዋስውን ማስተማር ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የሰዋስው ትምህርት ተግባራት በእውናዊነት ላይ የተመሠረቱ ከሆነ ተግባቦቱ የበለጠ ውጤታማ ይሆናል፡፡ በመማርያ ክፍሉ ውስጥ ሰዋስው ትምህርት ተግባራት በሚቀረፁበት ጊዜ እውነናዊነትን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ሲሆን የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት ለማጎልበት ተመራጭ ነው(Brown 1994)፡፡

በአጠቃላይ እውናዊት በቋንቋ መማርያ መፃሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ተግባራት በሚቀርቡበት ጊዜ እውናዊ ለሆኑ ተግባራት ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም እውናዊ የሆኑ የሰዋስው ትምህርት ተግባራትን በመጠቀም የቋንቋ ትምህርትን የምናስተምር ከሆነ ተማሪዎች በቋንቋው የመግባባት ክህሎታቸውን በእውኑ ዓለም ላይ ክፍል ውስጥ በበለጠ ሁኔታ እንዲጠቀሙበት ሊያደርጋቸው የሚችል መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

በአጠቃላይ በቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ከሰዋስው ትምህርት አቀራረብ አንጻር ኢታዩ እውናዊነትና የቋንቋውን ሥርዓት ፍቺና አገልግሎት እንዲሁም ለተማሪ ተኮርና ለሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ትኩረት የሚሰጡ ከሆነ ተማሪዎች ያላቸውን ሃሳብና ስሜት በትክክል እንዲገልፁ ከማድረግም በላይ የቋንቋውን ሥርዓት ፍቺና አገልግሎት አቀናጅቶ ለማስተማር የሚመቹ በመሆኑ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ብቃት ለማጎልበት አዎንታዊ የሆነ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡

### 2.1.3 በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀት

በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀትን በተመለከተ እንደ ማረው (2003፡7) አገላለፅ በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ቃላት ሲደራጁ በአንድ አጋጣሚ ተማሪዎች ተምረዋቸው በሌላ አጋጣሚ የሚያገኟቸው ወይም የማይጠቀሙባቸው ከሆነ የሚረሱ ስለመሆናቸው የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ቃላት በትውስታ ውስጥ መሠረታቸውን እንድጥሉና እንዳይረሱ ዙር መጥ (Recycling) በሆነ መንገድ ለተማሪዎች መቅረብ አለባቸው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ (Rechards, 2005:14) ደረጃውን ጥልቅ (Steep) መካከለኛ (Average) ነው ወይስ ግልብ (Shallow)፣ እድገቱ ቀጥተኛ ነው ወይስ ኡደታዊ በቂ

የሆነ የሰዋስው ድግግሞሽ አለ? አዲስ ሰዋስዋዊ መዋቅሮች እርስ በርስ ምን ያህል ተያያዥነት ወይም ዝምድና አላቸው? ለልምምድ የቀረበው መልመጃ ለምሳሌ ቃለ ምልልስ ሚና ነጠቃ ምን ያህል አስፈላጊ ነው? የሰዋስው መልመጃዎች በሚደራጁበት ጊዜ ለጀማሪዎች ሳይሆን ከዚህ በፊት ተማሩትን መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ ከሆነ የኮርሱን ደረጃ ፈጣን፣ (Steeply Grade) የሚለውን መርህ የተከተለ ነው፡፡ ነገር ግን አንድ የሰዋስው መልመጃዎች በተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ በተደጋጋሚ የሚቀርብ ከሆነ በተለይም ለጀማሪ የፈጣን ዕድገት ማሳየት ለሚሳናቸው ተማሪዎች ጥልቅ ያልሆነ ደረጃ (Shallow grading) ተስማሚ ነው ይላሉ፡፡ የኡደታዊ መርህ (Principle of recycling) ማለት ለምሳሌ ቃላት በተለያየ አውድ ውስጥ ተደጋግመው ከመጡ ተማሪዎች የቃሉን ቅርፅ፣ ድምፅና ፊደል በመረዳት ሙሉ ትርጉም እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል፡፡

ከምሁራን ሀሳብ እንደምንረዳው ለአንድ ለተወሰነ ክፍል መማሪያ እንዲሆን የተዘጋጀ መፃህፍ ለትምህርት የቀረቡ ልዩ ልዩ ጉዳዮች የተመጣጠኑ እንዲሆኑ ማለትም አንዱ ዘርፍ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶ ሌላው ዘርፍ ችላ እንዳይባል ወይም በንባብ ውስጥም ቢሆን ለቃላት ትርጉም ትኩረት ተሰጥቶ የአገላለፅና የሀሳብ አደራደር ጉዳይ ችላ እንዳይባል ሊመራ እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን በመማሪያ መጻህፍት ዝግጅት የተለያዩ መመዘኛዎችን መተግበር እንደሚስፈልግ ቢያስቀምጡም ተስፋዬ (1981) ሥነ-ልሳንና ቋንቋን ማስተማር በሚለው መጻህፋቸው እንዲሁም Tyler (1949) ከዚህ በፊት መሠረታዊ የሥርዓተ ትምህርት መርሆዎችና መመሪያዎች በሚለው መፅሐፋቸው ያካተቷቸው የተገቢነት መስፈርቶች ተገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ተስፋዬ (1981) ሥነ-ልሳንና ቋንቋን ማስተማር በሚለው መፅሀፋቸው ያካተቷቸውን የትምህርት ልምዶች በእነዚህ ምሁራን ሥራዎች ተገልፀዋል፡፡ እንደ Tyler (1949) እና ተስፋዬ (1980) ተከታታይነት፣ ተለጣጣቂነትና ውህደት ናቸው፡፡ እነዚህ መመዘኛ ነጥቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

#### 2.1.3.1 ተከታታይነት

በመማሪያ መጻህፍት ዝግጅት ሂደት የማደራጀት መስፈርት አንዱ ተከታታይነት ሲሆን ተከታታይነት የሚለው የሚያመለክተው በአንድ የትምህርት ዓይነት ውስጥ እያደገ ግን በተደጋጋሚ የሚመጣ ዓላማ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በቋንቋ ውስጥ ንባብን ከአንደኛ ክፍል ጀምረን እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ እናስተምራለን፡፡ ይህ ንባብና የማስተማር ጉዳይ እየተደጋገመ

የሚመጣ ነው። ነገር ግን ተማሪዎች ደረጃውን የጠበቀ የምንባብ ችሎታ እንዲያገኙ የዚህ ትምህርት አወቃቀርና ተገቢውን ስልት መያዝ አለበት። ይህንንም ሀሳብ Nunan (1991) እንደሚጠናክሩት ተመሳሳይ የሆኑ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሳይዘበራረቁ ወይም ሳይቆራረጡ በየክፍል ደረጃዎች እንደተማሪዎቹ ማንነት ተሳስረው መሄድ የሚችሉ ከሆነ የተማሪዎች ግንዛቤ በሂደት እንደሚጨምር አስተዋፅኦ ያደርጋል።

### 2.1.3.2 ተለጣጣቂነት

የመማሪያ መጻሕፍትን ስፋትና ጥልቀት በተለያየ መንገድ በማደራጀት የትምህርት ይዘቶቹ በአንድ የክፍል ደረጃ ላይ በተደጋጋሚ ማቅረብ ከተቻለ ተማሪዎቹ ተመሳሳይ የትምህርት ይዘቶችን በተለያዩ ምዕራፎች ላይ ማግኘት የሚችሉ በመሆኑ ይዘቱን በጥልቀት እንዲረዱት ያደርጋል (Tyler (1949)። አያይዘውምተስፋዬ (1981) ተለጣጣቂነት ከተከታታይነት የሚዛመድ ቢሆንም የሚለይበት ባህሪ አለው። ይኸውም በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የሚቀርብ የትምህርት ጉዳይ በየደረጃው ስፋትና ጥልቀት እያገኘ እንዲሄድ የሚመራ ነው። በአንድ መጻህፍት ልዩ ልዩ ምዕራፎች መካከልም ሆነ በተለያዩ ክፍሎች በተዘጋጁ መጻህፍት መካከል ተለጣጣቂነት የቅደም ተከተል ጉዳይ ነው። በባህሪያት ትንታኔ ውስጥ ተለጣጣቂነት ሲባል ይኸው ነው። በአንድ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ባሉ ልዩ ልዩ ምዕራፎች መካከልና በተለያዩ ክፍሎች የመማሪያ መፃህፎች መካከል ተለጣጣቂነት እንዲኖር ያስፈልጋል። በመሠረቱ ተማሪው በሚያደርገው የመማር ጥረት በጊዜው እያደገ የሚሄድ መሆኑን መገንዘብ አለበት። ቀጥሎም የሚደርስበት ምዕራፍ ካለፈው የተለየና ያደገ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት። ያለፈውን የሚደግም ከሆነ ግን እድገት ወይም አዲስነት የለምና ማሰላቸት ያስከትላል።

ይህ ማለት ተመሳሳይ የሆኑ የትምህርት መልመጃዎችን በአንድ የክፍል ደረጃ ላይ በተለያየ አቀራረብ በተደጋጋሚ ማቅረብ መቻል የተለጣጣቂነት ፅንሰ ሀሳብ መሆኑን መረዳት ይቻላል። በዚህ መልኩ የመማሪያ መጻህፍት መደራጀት ከቻሉ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ተመሳሳይ የትምህርት መልመጃዎችን በተለያዩ ምዕራፎች ላይ ማግኘት የሚችሉ በመሆኑ ይዘቱን በጥልቀት እንዲረዱት አስተዋፅኦ የሚያደርጋቸው መሆኑን ለመግለጽ ነው።

### 2.1.3.3 ውህደት

ውህደት የሚባለው ደግሞ በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ያሉትን የትምህርት ልምዶች መሠመራዊ ግንኙነት የሚመለከት ነው። የተዋሃዶ የትምህርት ልምዶች የእርስ በርስ መደጋገፍ አንዱ ሌላውን ማዳበርና የማበልጸግ ጉዳይ ነው። ለምሳሌ በ9ኛ ክፍል የሚሰጠው

የአማርኛ ትምህርት በ9ኛ ክፍል ከሚሰጠው የህብረተሰብ ትምህርት ጋር እንዲዛመድ የተደረገ እንደሆነ አንዱ ሌላውን የሚያጎለብት ይሆናል(ተስፋዬ1981)፡፡ ይህንንም ሀሳብ Tyler(1949) በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች መካከል ያለውን ጎናዊ ግንኙነት በማጤን የማደራጀት ተግባር የሚከናወንበት ሂደት ነው፡፡ በተለያዩ ሁለት ቋንቋዎች ውስጥ ያሉ የትምህርት ይዘቶችን በተመሳሳይ የትምህርት ወቅት የመማር ማስተማሩ ሂደት ሲከናወን ተማሪዎቹ ከሁለቱም የትምህርት ዓይነቶች ተቀራራቢ ዕውቀት ወይም ክህል በመኖሩ ግንዛቤያቸው እንዲሰፋ ያደርጋል፡፡

ከሀሳቡ መረዳት እንደሚቻለው ተመሳሳይ የክፍል ደረጃ በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች መካከል ያለውን ጎናዊ ግንኙነት በማጤን የማደራጀት ተግባር የሚከናወንበት ሂደት መሆኑን ነው፡፡

በአጠቃላይ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ሲዘጋጁ የመልመጃ አደረጃጀታቸው በከፍተኛ ጥናትና ጥንቃቄ ሊከወን ይገባል፡፡ አካሄዱም ከሚታወቅ ወደማይታወቅ፣ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከግልፅ ወደ ውስብስብ፣ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ መመራት እንደሚኖርበት ለመግለጽ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.1.4 የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ምንነት

የተለያዩ ምሁራን የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ምንነት በተለያየ መንገድ ሲገልፁ የሚታይ ቢሆንም በብያኔያቸው የሚያነሷቸው ነጥቦች ተመሳሳይነት አላቸው፡፡

እንደ Grant (1987:5) የመማሪያ መጻሕፍት የተማሪውን የትምህርት ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ፍላጎት፣ የትምህርት ዓላማዎችን የያዘ፣ ለአላማዎቹ ማስፈፀሚያ የሚሆኑ ተመጣጣኝ፣ ተለጣጣቂና ተደጋጋፊ ይዘቶች በውስጡ አደራጅቶ የያዘ ለክፍል ማስተማሪያነት የሚያገለግል መሣሪያ ነው፡፡

ከምሁራን ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው የመማሪያ መጻሕፍት በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችንና መምህር በማስተሳሰር የትምህርት ሥርዓቱን ፈር የሚያስይዝና የሚመራ ነው፡፡ እንዲሁም የመማሪያ መፃህፍ ለየትኛው ተማሪና ለየትኛው ክፍል ተብሎ በመለየት ደረጃውን ለሚመጥን ክፍል የሚዘጋጅ መሆኑን እንረዳለን፡፡ በተጨማሪም እንደ ዋነኛ የእውቀት ምንጭ ወይም የመረጃ ስብስብ ሆኖ የተማሪውን ግንዛቤ አድማስ ለማስፋት የሚያግዝ መሳሪያ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

እንደ ተስፋዬ (1981፡43) ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ማስተማሪያ የሚሆኑ ደረጃቸውን የጠበቁ መጻህፍት ማግኘት የመምህራን ሥራ የሚያጠነክር ይሆናል፡፡ ተማሪው የተለያዩ መጻህፍትን ሲያነብ ከተለያዩ ይዘቶች ጋር ለመተዋወቅ ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ የአፃፃፍ ስልቶችም ጋር ለመተዋወቅ ይረዳል፡፡ በዚያውም ልክ አስተሳሰቡ ሲሰፋ የቋንቋ ችሎታው ሊዳበር ይችላል ይላሉ፡፡ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የመማሪያ መጻህፍት የማይተካ ሚና ቢኖራቸውም እነዚህ መጻህፍትን የሚያይዝና የሚዳብሩ ተጨማሪ ጽሑፎች፣ መልመጃዎች ሌሎችም አጋዥ የማስተማሪያ መሣሪያዎች በመማር ማስተማሩ ውጤታማ ያደርጋል፡፡

በአጠቃላይ በተለያዩ ምሁራን ሥራዎችና መዝገበ ቃላት የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ምንነት በሚመለከት የተሰጡ ትንታኔዎች ሲታዩ መፃህፍቱ የቋንቋ ትምህርት ዓላማን መሠረት ያደረጉ፣ በሥርዓተ ትምህርቱና በመርሃ ትምህርቱ ዝግጅት ላይ የተመሠረቱ የግብ መምቻ ሰነዶች ናቸው፡፡ ተመጣጣኝ፣ ተደጋጋፊ፣ ተለጣጣቂና ውህደት ያለው በተመረጡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ላይ ተመስርተው አደረጃጀታቸውና አቀራረባቸው አራቱን ክህሎቶችና የሥነ-ልሣን የሥነ-ጽሑፍ እውቀትን ለማስተላለፍ የሚችሉ የተግባር መልመጃዎችን የያዙ መሣሪያዎች መሆናቸውን እንረዳለን፡፡

### 2.1.5 የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያለው ግንኙነት

የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት እና መርሃ ትምህርቶቹ ያላቸውን ግንኙነት የተለያዩ ምሁራን ብያኔ ሰጥተዋል፡፡ እንደNunan (1989) ገለፃ መርሃ ትምህርት ጠባብ የሆነ አተያይ ያለው ከመሆኑም በላይ በይዘቶች መረጣና አደረጃጀት ላይ ስለሚያተኩር ሙሉ በሙሉ በአርዕስቶች (Topic based) ላይ የተመሠረተ የሥርዓተ ትምህርት አንዱ ክፍል ነው፡፡ መማሪያ መጻሕፍት ማለት ደግሞ መርሃ ትምህርቱን መሠረት በማድረግ የሚቀረፅና ከቋንቋው ትምህርት አንፃር ሲታይ በውስጡ የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት ሊያጎለብቱ የሚችሉ የተለያዩ የዕውቀትና የክህሎት ዘርፍ ይዘቶችን ስርዓታዊ በሆነ በማደራጀት አካቶ የሚይዝ ሠነድ ሲሆን አብዛኛው መምህራን መርሃ ትምህርት ማለት መማሪያ መፅሐፍ ነው ብለው ስለሚያስቡ መማሪያ መፅሐፍ ማለት በስርዓተ ትምህርት ውስጥ የተገለፁትና ተጨባጭ ሆኑ ገፅታዎች የሚንጸባረቁበት መሣሪ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡ ይህንን ሀሳብ አያይዘውም Cunningworth (1995) በበኩላቸው መርሃ ትምህርት በአንድ የትምህርት ዓይነት ወይም የክፍል ደረጃ የሚሸፍን የትምህርት ርዕስ የሚገለፅበት ነው፡፡ በእያንዳንዱ ክፍል የሚቀርበው

የጊዜ ወሰን፣ የትምህርት አቀራረብ፣ ዘዴና ልምምድ የሚደረግበት ሂደት በማያሻማ መንገድ የሚቀርብበት ነው፡፡

በአጠቃላይ የመርሃ ትምህርት ይዘቶች መነሻቸው ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀው መርሃ ትምህርት እንደሆነ ይዘቱም በመርሃ ትምህርቱ የተጠቀሱትን የትምህርት ዓላማዎች ሊያሳኩ የሚችሉ የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ፍላጎት መሠረት ያደረጉ ግልፅና ጠቃሚ መሆን እንዳለባቸው ከመማሪያ መፅሐፉ ጋር ግንኙነት እንዳለው ከላይ ከቀረበው ገለጻ መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ የሚጠናው ጥናት ተዛማጅ ከሆኑ ቀደምት ጥናቶች ጋር ሲነፃፀር በምን እንደሚመሳሰልና እንደሚለያይ በዝርዝር የሚዳሰስበት ክፍል ሲሆን፤ ይህ ጥናት ከቀደምት ጥናቶች ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት እንደሚከተለው ለማቅረብ ይሞከራል፡፡

ሰላም (2010፣ ሰሚራ (2010)፣ ተስፋዬ (1993) የሰዋስው ትምህርት ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ናቸው፡፡

የመጀመሪያ ሰሚራ (2010) ጥናታዊ ጽሑፍ በደቡብ ክልል በ2009 ዓ.ም ሥራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ የሰሚራ (2010) አቢይ ዓላማ በደቡብ ክልል በ2009 ዓ.ም ሥራ ላይ በዋለው የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ ይህ ጥናት ደግሞ በዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት መፈተሽ ነው፡፡ይህንን ዓላማ ለማሳካት የሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን የተሰበሰበው መረጃ በገላጭመተንተኛ ዘዴ ተተንትኗል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከሰሚራ (2010) ጥናት ጋር የሚመሳሰለው የይዘት አደረጃጀት መስፈርቶችን በመጠቀም ሰፊና የይዘት ድግግሞሽ የሚታይባቸው፣ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው የተደራጁ መሆናቸው፣ መማሪያ መፅሀፍ ላይ ያተኮረ ሲሆን የሚለያየው ደግሞ የሰሚራ (2010) በስምንተኛ ክፍል መማሪያ

መፅሀፍ ላይ ያተኮረ፣ ይዘቶች ላይ ያተኮረና የታተመበት ዓመተ ምህረት እንዲሁም የሰዋስው አቀራረብ የመገምገሚያ መስፈርቶች አጠቃቀም ስልት የተለየ በመሆኑ ነው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ሰላም (2010) ጥናታዊ ፅሑፍ በ2004 ዓ.ም ታትሞ ሥራ ላይ በዋለው የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አመራረጥና አደረጃጀት ከሥነ-ትምህርታዊ ሰዋስው አንፃር መመርመር ሲሆን ዓላማው በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አመራረጥና አደረጃጀት ከሥነ-ትምህርታዊ ሰዋስው አንፃር መመርመር የሚል ነው፡፡ ይህ ጥናት ከሰላም (2010) ጥናት ጋር የሚመሳሰለው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀታቸው እየጨመረ የሚሄድ አላስፈላጊ ድግግሞሽ የሚታይባቸው መሆኑ፣ እንዲሁም በአስረኛ ክፍል ላይ ትኩረት ማድረጉና የታተመበት ዓመተ ምህረት፣ መረጃዎችን ዓይነታዊ መተንተኛ ዘዴ መጠቀም ሲሆን የሚለያየው ደግሞ የሰላም (2010) ጥናት የትምህርት ይዘቶችን በይዘት ምርጫ መስፈርቶችና በሥነ-ትምህርታዊ አቀራረብ የመገምገሚያ መስፈርቶችን መጠቀም እንዲሁም ከሠነድ ፍተሻ በተጨማሪም ቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም በዓይነታዊ መረጃ የፈተሸ መሆኑ ነው፡፡

ሌላው ደግሞ ተስፋዬ (1993) ዓ.ም ያጠናው ጥናታዊ ፅሑፍ ተጠቃሽ ነው፡፡ ጥናቱ በስምንተኛ ክፍል አማርኛ ኢ-አፈ ፊት ተማሪዎች በተዘጋጀ የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ በሚል ርዕሥ ስሆን፤ ዓላማው በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል ማየት የሚል ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት ከተስፋዬ (1993) ጥናት ጋር የሚመሳሰለው የይዘት አቀራረብ መንገዶችን እና አደረጃጀት መንገዶችን መጠቀሙ ሲሆን የሚለያየው ደግሞ የተስፋዬ (1993) ጥናት በስምንተኛ ክፍል ኢ-አፈ ፊት ተማሪዎች ላይ ያተኮረ መሆኑና ከሠነድ ፍተሻ በተጨማሪ የጽሑፍ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን የተጠቀመ በመሆኑ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ጥናቶች ጋር ከተነሳው ርዕሰ ጉዳይ አንጻር የሚመሳስላቸው ነጥቦች ያሉ ሲሆን ጥናቱ በተከታታይ ባሉ ሁለት የክፍል ደረጃዎች ላይ የሚያተኩር ከመሆኑም በላይ የሰዋስው ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ላይ የሚያጠነጥን ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት፡-የጥናቱ ንድፍና ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2004 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር ታትመው በስራ ላይ በዋሉት የዘጠነኛና የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ያሉ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎችን አቀራረብና አደረጃጀት መፈተሽ ሲሆን፤ ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ ገላጭ የምርምር ንድፍ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

አጥኝዋ ገላጭ የምርምር ንድፍን የመረጠችበት ምክንያት ጥናቱ ከዚህ የምርምር ንድፍ ጋር የሚመሳሰል ስለሆነ ነው፡፡ ይህ ሲባል ገላጭ የምርምር ንድፍ አንድ ተመራማሪ የሚያጠናውን ጥናት እንዳለ ታሪካዊ በሆነ መልኩ በአንባቢ አእምሮ ውስጥ ስለ ጉዳዩ ስዕል በሚፈጥር ሁናቴባልተጋነነ እውነታን በማያደበዝዝ መልኩ ለማቅረብ የሚያስችል፤ በምርምር ዙሪያ ላይ ምን እየተካሄደ እንደሆነ የችግሩ ስፋት ምን እንደሆነና ምን እንደሚመስል ከመዳሰስ ውጪ ለምንና እንዴት ለሚሉ ምክንያታዊ ጥያቄዎች ትኩረት የማይሰጥ ነው በማለት (ያለው2004) ያብራራሉ፡፡

ስለሆነም ይህ ጥናት የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል በመፈተሽ ምንም ሳይጨምርና ሳይቀንስ ያለውን እውነታ ትርጉም በሚሰጥ መልኩ ለአንባቢያን ከማሳየት ውጪ ለምንና እንዴት ለሚሉ ጥያቄዎች ትኩረት የማይሰጥ በመሆኑ ነው፡፡

## 3.2 የናሙና አመራረጥ ስልት

በዚህ ንዑስ ክፍል ስለመማሪያ መጻሕፍቱ የናሙና አመራረጥ ስልት እና የጥናቱ የመረጃ ምንጮችይገለጻል፡፡

ጥናቱ የዘጠነኛና የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን፣ መጻህፍቱ የተመረጡት በዓላማ ተኮር የናሙና ስልት ነው፡፡ ዓላማ ተኮር የናሙና ስልትን በመጠቀም መማሪያ መጻህፍቱ የተመረጡበት ምክንያት በሁለቱም የክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎች በ2004 ዓ.ም በታተሙት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች መሠረት በማድረግ በክፍል ውስጥ የሚሰጣቸውን የቤት ሥራና የክፍል ሥራ ሲሰሩ ሀሳባቸውን በቃልና በፅሁፍ አቀናብረው መግለጽ የሚቸገሩ ብቻ ሳይሆን የቋንቋውን ፊደሎች እንኳን በትክክል የማይለዩ ተማሪዎች ያጋጠሟት በመሆኑ፤

እንዲሁም በተሰጣቸው የሰዋስው መልመጃ ላይ እርስ በርስ ያለመግባባት ችግር ሲገጥማቸው ያስተዋለች በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ይህን ችግር ከስሩ ለመመርመር  የዘጠነኛና የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ላይ በማተኮር በውስጣቸው የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ለመፈተሽ ዓላማ ተኮር የናሙና ስልት ተመራጭ ሆኗል፡፡

የጥናቱ የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለገሉትም፣ በዋናነት በሁለቱ የክፍል ደረጃ ያሉት የመማሪያ መጻህፍት ሲሆኑ፣ በደጋፊነት ደግሞ ለየክፍል ደረጃዎቹ የተዘጋጁት መርሃ ትምህርቶች ናቸው፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰያ ስልት

የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ከመረጃ መሰብሰብያ ስልቶች ውስጥ ሰነድ ፍተሻጥቅም ላይ ውሏል፡፡ሰነድ ፍተሻ በአጥኚዋ አማካኝነት የተካሄደ ሆኖ አሁን በሥራ ላይ ያለውን  የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መጻህፍት በመውሰድ በሠነድነት ይፈትሸዋል፡፡ ይህም ለአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ትግበራ ተዘጋጅተው በቀረቡት መጻህፍት ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው መልመጃዎች አቀራረባቸውንና አደረጃጀታቸውን ለመፈተሽ  ያስችላል ከሚል እሳቤ ነው፡፡

## 3.4 የመረጃ መተንተኛ ስልት

ከመማሪያ መፃህፍቱ በሠነድ ፍተሻ የተገኙትን መረጃዎች በተለያዩ ንዑሳን ርዕሶች በመከፋፈል ገላጭ የአተናተን ዘዴን በመከተል ለመተንተን ይሞከራል፡፡ ይህም የዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት የሚዳሰሱ መረጃዎችን በዓይነት ከተለዩ በኋላ በንዑሳን ክፍሎች በመከፋፈል ገላጭ የአተናተን ስልትን በመከተል እንዲቀርብ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

የሰዋስው አቀራረብና አደረጃጀትን ማለትም የሰዋስው አደረጃጀት ከተከታታይነት፣ ከውህደት፣ ከተለጣጣቂነት አንፃር የሚዳሰስ ሲሆን ከሰዋስው አቀራረብ አንፃር ደግሞ የጥንታዊና የዘመናዊ በሚል የሰዋስው አቀራረብ መንገዶች የቀረበ ነው፡፡ ከሰዋስው አቀራረብ መገምገሚያ መስፈርቶች ደግሞ የቋንቋውን ሥርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት አቀናጅቶ ከማቅረብ አንፃር፣ እውናዊነትን ተላብሶ ከማቅረብ አንፃር ተማሪ ተኮርና ሂደት ተኮር አቀራረብን መሠረት በማድረግ ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡

# ምዕራፍ አራት፡-የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

## 4.1 የመረጃትንተና

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2004 ዓ/ም ተሻሽለው በተዘጋጁት የዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀትን መገምገም ሲሆን፤ የዚህን ጥናት ዋና ዓላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ ከመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች ውስጥ ሰነድ ፍተሻን በመጠቀም ለመገምገም ተሞክሯል፡፡

በዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች በምን መልኩ እንደቀረቡና የአደረጃጀት ተገቢነትን በመፈተሽ የመፅሐፍቱን መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀትን ምሁራን ከሚያስቀምጧቸው ንድፈ ሀሳቦች በመነሳት እና መስፈርቶችን በየዘርፋቸው በመተንተን ግልፅ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ በሠነድ ፍተሻ የተገኙ ውጤቶችን ከምሁራን ንድፈ ሀሳባዊ እይታና ከቀደምት የጥናት ውጤቶች አንፃር ማብራሪያ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

በመሆኑም የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፀሐፍ በውስጡ ሶስት የትምህርት ይዘቶችንና 10 ምዕራፎችን በ185 ገፅ አካቶ የያዘ መማሪያ መጻሕፍት ነው፡፡ በመማሪያ መፃህፍፉ ውስጥ የተካተቱት መልመጃዎች ሰዋስው፣ ስነ-ፅሑፍና ክህሎት ሲሆኑ፤ በሁሉም ምዕራፎች ውስጥ በክህሎት ላይ የሚያተኩሩ ናቸዉ፡፡ ሰዋስውና ስነ-ፅሑፍ ደግሞ ከአንደኛው፣ ከሶስተኛውና ከአስረኛው ምዕራፍ ውጪ በቀሪዎቹ ሰባት ምዕራፎች ውስጥ ተካተው ይገኛሉ፡፡

በተመሳሳይ የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ በውስጡ ሶስት የትምህርት ይዘቶችንና አስር ምዕራፎችን በ147 ገፅ አካቶ የያዘ መማሪያ መፅሐፍ ነው፡፡ በመማሪያ መፃህፍ ውስጥ የተካተቱት የትምህርት ይዘቶች ሰዋስው፣ ስነ-ፅሑፍና ክህሎት ሲሆኑ በሁሉም ምዕራፎች ውስጥ ሁሉም የትምህርት ይዘቶች ተካተው ይገኛሉ፡፡

በመጨረሻ የዚህ ጥናት ማጠንጠኛ መስፈርት የሆነው የሰዋስው መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀትን በተመለከተ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች በየመፃህፍቱ ምዕራፍ በንዑስ ክፍል ደረጃ ሰዋስው በሚል ራሱን የቻለ አርዕሥት ለተማሪዎች የቀረቡ ሲሆን፤ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍ በአጠቃላይ ሰዋስውን የተመለከቱ ከ10 ምዕራፎች ውስጥ ምዕራፍ 2 በገፅ 24፣ ምዕራፍ 4 በገፅ 67፣ 68፣ 69፣ በምዕራፍ አምስት በገፅ 86፣ በምዕራፍ

ስድስት በገፅ 109፣ ምዕራፍ 7 በገፅ 128፣ ምዕራፍ 8 በገፅ 141፣ 143፣ ምዕራፍ 9 በገፅ 155 ላይ ተካተው ይገኛሉ፡፡

በተመሳሳይ የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍ በአጠቃላይ ሰዋስውን የተመለከቱ ከአስር ምዕራፎች ውስጥ በምዕራፍ አንድ በገፅ 14፣ በምዕራፍ ሁለት በገፅ 27፣ በምዕራፍ ሶስት በገፅ 44፣ 45 በምዕራፍ አራት በገፅ 60፣ 61 በምዕራፍ አምስት በገፅ 73፣ በምዕራፍ ስድስት በገፅ 83፣ 86 በምዕራፍ ሰባት በገፅ 96፣ በምዕራፍ ስምንት በገፅ 114፣ በምዕራፍ ዘጠኝ በገፅ 124፣ 125 እንዲሁም በምዕራፍ አስር በገፅ 139 ላይ ተካተው ይገኛሉ፡፡ ት.ሚ (2004)፡፡

ሠንጠረዥ "ሀ". በዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ የሰዋስውመልመጃዎች

| ምዕራፍ | **በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች** | **በአሥረኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች** |
|---|---|---|
| ምዕራፍ (1) | - | የተዘረዘሩትን ቃላት በነፃና ጥገኛ ምዕላድ መለየት |
| ምዕራፍ (2) | የተዘረዘሩትን ቃላት በነፃና በጥገኛ ምዕላድ መለየት | መሪ ቃሉን በመጠቀም ሀረግ መመስረትና የሀረግ አይነቶችን መለየት |
| ምዕራፍ (3) | - | የአያያዥና የመሸጋገሪ ቃላት፣ የዐ.ነገር አይነቶች እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች መለየት |
| ምዕራፍ (4) | -የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች መስጠት<br>-የተሰመረባቸው ቃላት ከየትኛው የቃል ክፍል እንደሚመደቡ መለየት | መስራች ምዕላድና የዐ.ነገር ስልቶችን መለየት |
| ምዕራፍ (5) | የዐ.ነገር ክፍሎችን መለየት | የሀረግ አመሠራረትና ውስብስብ ዐ.ነገሮችን መመስረት |
| ምዕራፍ (6) | ነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን መለየት | ምዕላድ፣ አገባባዊ ፍች የቃላት መጥበቅና መላላት |
| ምዕራፍ (7) | የቃል ክፍሎችን መለየት፣ ዐ.ነገር መመሥረት | የቃላት ቀጥተኛ ፍች መስጠት |
| ምዕራፍ (8) | የስማዊ ሀረግና ቅፅላዊ ሀረግ አመሰራረት | የሀረግ ኤነቶችንና የአ.ነገር አይነቶችን መለየት |
| ምዕራፍ (9) | የቃል ክፍሎች ሙያዎች መለየት | የዐ.ነገር ስልትና ምዕላድን መለየት |
| ምዕራፍ (10) | - | ተራ እና ውስብስብ ዐ.ነገር መሥራትና መስራች ምዕላዱን መለየት |

በአጠቃላይ በሁሉቱም የትምህርት ደረጃዎች በርካታ ሰዋስው ትምህርት መልመጃ ያላቸው ሲሆን የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በሰባት ምዕራፎች ምዕላድን የተመለከቱ የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች መነሻና መድረሻ ቅጥያዎች ቃል ነፃ ምዕላድ፣ ጥገኛ ምዕላድ፣ ስማዊ ሀረጎች የቃል ክፍሎች ሙያዎች እና የቃላት መጥበቅና መላላት ተመለከቱ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡

በተመሳሳይ የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በሁሉም ምዕራፎች ምዕላድን ተመለከቱ፣ የቃላትና የሀረጋት አይነቶች አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት፣ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች፣ የቃላት መጥበቅና መላላት፣ አገባባዊ ፍችን የተመለከቱ የሰዋስው መልመጃዎች ተካተዋል፡፡

### 4.1.1 በዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው መልመጃዎች አቀራረብ

በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ አቀራብ የተማሪዎችን ማንነት ባገናዘበ መልኩ ከማቅረብ ባለፈ አቀራረቡም በተለየዩ የማስተማሪያ ዘዴ የተቃኘ መሆን እንደሚገባው ይታመናል፡፡ ስለሆነም ከላይ በምዕራፍ ሁለት የተገለጹትን የአቀራረብ መስፈርቶች መሠረት በማድረግ የተገኘውን መረጃ በንዑስ ርዕስ በመከፋፈል ከዚህ በታች እንደሚከተለው በሠንጠረዥ መልክ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

#### 4.1.1.1 በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍት የቋንቋውን ስርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት አቀናጅቶ ከማቅረብ አንጻር

በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ከአቀራብ አንፃር የመገምገሚያ መስፈርት የሆነው የቋንቋውን ስርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት አቀናጅቶ ከማቅረብ አንፃር ነው፡፡ ስለዚህ በመማሪያ መፅሐፍቱ ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው መልመጃዎች መስፈርቱን የማያሟሉ ከዚህ በታች በሠንጠረዥ ተለይተው ቀርበዋል፡፡

ሠንጠረዥ “ለ”፡- በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍ ሰዋስው መልመጃዎች የቋንቋውን ሥርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት አቀናጅቶ ከማቅረብ አንጻር

በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቋንቋውን ሥርዓት ፍቺና አገልግሎት አቀናጅቶ ከማቅረብ አንጻር ሰፊውን ቦታ የያዘው የቋንቋው ስርዓት ወይም ቅርፅ እንደሆነ ለማየት ተችሏል፡፡ ለዚህም እንደ ማሳያ ሊሆን የሚችል ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች የቋንቋውን ስርዓት ፍቺና አገልግሎት አቀናጅቶ ከማቅረብ አንፃር | | የድግግሞሽ መጠን | |
|---|---|---|---|---|
| | | ገፅ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ሥርዓት (ቅርጽ) | 24፣69፣70፣86፣109፣155 | 6 | 54.5 |
| 2 | ፍቺ | 44፣67፣143 | 3 | 27.3 |
| 3 | አገልግሎት | 128፣156 | 2 | 18.2 |

በሠንጠረዥ "ለ" ከቀረበው መረጃ እንደምንረዳው ከሆነ በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ላይ ከቀረቡት 11 የሰዋስው መልመጃዎች ውስጥ 6 ወይም (54.5%) የሚሆኑ የሰዋስው መልመጃዎች ለስርዓቱ ትኩረት የሚሰጡ ሲሆኑ 3 ወይም (27.3%) የሚሆኑት የሰዋስው መልመጃዎች ለፍቺ ትኩረት የሚሰጡ ናቸው፡፡ እንዲሁም 2 ወይም (18.2%) የሰዋስው መልመጃ ደግሞ ለአገልግሎቱ ትኩረት የሚሰጥ ነው፡፡ ስለዚህ በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች የቋንቋውን ሥርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት ከማቅረብ አንጻር በመቶኛ ስሌት ሲታዩ አብላጫውን ድርሻ ማለትም (54.5%) የሚሆነውን የያዙት በስርዓቱ ላይ ብቻ ተንተርሰው የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች ናቸው፡፡ ይህንንም ሀሳብ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ 24፣69፣70፣86፣109፣155 ላይ የቀረቡትን ስድስት ሰዋስው መልመጃዎችን በአስረጅነት በመውሰድ እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

በምዕራፍ አራት በገፅ "69" ላይ የቀረበውን ጥያቄ ቁጥር አራትን ስንመለከት የሚከተሉት ዐ.ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት ከየትኛው የቃል ክፍል እንደሚመደቡ (የቃል ክፍላቸውን) ግለጽ፡፡

1. አየለ መኪና <u>ገዛ</u>፡፡
2. መንኮራኩሯ <u>ጨረቃ</u> ላይ አረፈች፡፡
3. <u>ሰነፍ</u> ሰው ሥራን አይወድም ፡፡
4. ዛሬ <u>ስለ</u>መሬት ተማርኩ፡፡

የሚሉ ሲሆን በምዕራፍ አምስት በገጽ “86” ላይ የቀረበውን ጥያቄ ቁጥር አንድን ስንመለከት ደግሞ ከላይ በተገለጸው ምሳሌ መሠረት፣ በሚከተሉት ዐ.ነገሮች ውስጥ ያሉትን ባለቤት፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀፆችን አውጡና በሠንጠረዥ አሳዩ፡፡

1. ግንበኛው ድንጋዩን ፈለጠ፡፡
2. ጎርፉ ዛፉን ገነደሰው፡፡
3. መቅደስ በሩን ቀጠቀጠችው፡፡
4. መምህራኑ ቤት ገዙ፡፡
5. ዶሮዎቹ እንቁላል ጣሉ፡፡
6. አክስቴ የጠላውን አተላ ደፋችው፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በምዕራፍ ስድስት በገፅ “109” ላይ የቀረበውን ጥያቄ ቁጥር ሶስትን ስንመለከት ደግሞ የሚከተሉትን ቃላት በነፃና በጥገኛ ምዕላድ ከፋፍሉ፣ ሙከራችሁንም ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማቅረብ ተነጋገሩባቸው፡፡

<u>**ምሳሌ**</u>፡- ሰዎች፣ ሰው -ኦች

| ነፃ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ |
|---|---|
| 1. ገበሬዎች | 5. ባርኔጣዎች |
| 2. ወንድሟ | 6. አገሯ |
| 3. ስሙ | 7. ገንዘቧ |
| 4. በናትህ | 8. ደብተርሽ የሚሉ ናቸው፡፡ |

ከዚህ በላይ የቀረቡት ሶስት መልመጃዎችን ስንመለከት በምዕራፍ አራት በገፅ “68” በጥያቄ አራት ላይ የቀረበው የሰዋስው መልመጃ ተማሪዎች በዐ.ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት ከየትኛው የቃል ክፍል እንደሚመድቡ (የቃል ክፍላቸውን) እንዲገልፁ ብቻ የሚያደርግ ነው፡፡ በምዕራፍ አምስት በገፅ “86” በጥያቄ ቁጥር አንድ ላይና በምዕራፍ ስድስት በገፅ “109” በምዕራፍ አራት በገፅ “68” በጥያቄ ቁጥር አራት ላይ ከቀረበው የሰዋስው መልመጃ የተለየ አቀራረብ የላቸውም፡፡ ምክንያቱም በምዕራፍ አምስት በገፅ “86” በጥያቄ ቁጥር አንድ ላይ የቀረበውን የሰዋስው መልመጃ ተማሪዎች በዐ.ነገሮች ውስጥ ያሉትን ባለቤት፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀፆችን እያወጡ በሰንጠረዥ ብቻ እንዲገልፁ የሚያደርግ ሲሆን በምዕራፍ ስድስት በገፅ “109” በጥያቄ ቁጥር ሶስት ላይ የቀረበውን የሰዋስው መልመጃ ደግሞ ተማሪዎች በዝርዝር የቀረበላቸውን ቃላት ነፃና ጥገኛ ምዕላድ እያሉ እንዲከፋፍሉ ከማድረግ ውጪ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ብቃት ለማጎልበት የቋንቋውን ሥርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት በተቀናጀ ሁኔታ

እንዴት፣ የትና መቼ መጠቀም እንደሚገባ የማያሳዩ ስለሆነ ነው፡፡ሠንጠረዥ “ሐ” በአስረኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ የቀረበውን ስርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት  አቀናጅቶ ከማቅረብ አንፃር በአስረኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ከቋንቋው ስርዓት ፍቺና አገልግሎት አንጻር ሲታዩ ዝቅተኛውን ቦታ ይዞ የሚገኘው የቋንቋው ፍቺና አገልግሎት ሲሆኑ ለዚህም ማሳያ ሚከተለውን ሠንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡

| ተ.ቁ | በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች የቋንቋውን ስርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት ከማቅረብ አንፃር | ገፅ | በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሥርዓት (ቅርጽ) | 14፣26፣45፣60፣72፣ 83፣114፣125፣139 | 9 | 69.4 |
| 2 | ፍቺ | 45.96 | 2 | 15.3 |
| 3 | አገልግሎት | 124 | 2 | 15.3 |

በሠንጠረዥ ”ሐ” ከቀረበው መረጃ እንደምንረዳው ከሆነ በአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ላይ ከቀረቡት 13 የሰዋስው መልመጃዎች ውስጥ 9 ወይም (69.4%)የሰዋስው መልመጃዎች ለስርዓቱ ትኩረት የሚሰጡ ሲሆን 2 ወይም (15.3%) የሚሆኑት የሰዋስው መልመጃዎች ለፍቺ ትኩረት የሚሰጡ ናቸው፡፡ እንዲሁም 2(15.3%) የሚሆኑ የሰዋስው መልመጃዎች ደግሞ ለአገልግሎቱ ትኩረት የሚሰጥ ነው፡፡

ስለዚህ በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች የቋንቋውን ፍቺ፣ ስርዓት እና አገልግሎት አንፃር በመቶኛ ስሌት ሲታዩ አብላጫውን ድርሻ ማለትም (69.4%) የሚሆነውን የያዙት በስርዓቱ ላይ ብቻ ተንተርሰው የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች ናቸው፡፡ ይህንን ሀሳብ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ገፅ 14፣ 26፣45፣60፣72፣83፣114፣125፣139 ላይ ቀረቡትን ከዘጠኝ የሰዋስው መልመጃዎች ውስጥ በአስረጅነት ሶስት የሚሆኑ ገፆችን ለመውሰድ ተሞክሯል፡፡ በምዕራፍ አራት በገፅ 61 ላይ የቀረበውን ስንመለከት ከላይ የተሰጠውን ምሳሌ በመመልከት ቀጥሎ የተሰጡትን ግሶች ወደ ቅፅል ቀይራችሁ አሳዩ

**ግስ** **ቅፅል**

1. ጎተተ
2. ባከነ
3. ደነደነ

4. አሽገ

5. ተለቀ

የሚሉ ሲሆን በምዕራፍ አስር በገፅ “139” ላይ የቀረበውን መልመጃ ስንመለከት ደግሞ ከዚህ ቀደም ባሉት ምዕራፎች ከግስ የተለያዩ ስም መሰል ቃላትና ቅፅሎችን መመስረት እንደሚቻል ተምራችኋል፡፡ ምሳሌውን በመከተል ስሩ፡፡

| | ግስ | ከግስ የተመሠረተ ስም መሰል ቃል | ከግስ የተመሠረተ ቅፅል |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ፡- | ቀጠፈ | መቅጠፍ | ቀጣፊ |

1. ሰነፈ
2. ሰከረ
3. ዘለለ
4. ቀለለ
5. በላ

ከዚህ በላይ የቀረቡትን ሁለት መልመጃዎችን ስንመለከት በምዕራፍ አራት በገፅ “61” ላይ የቀረበው መልመጃ ስንመለከት ከላይ የተሰጡትን ምሳሌ በመመልከት ቀጥሎ የተሰጡትን ግሶች ወደ ቅፅል እንዲቀይሩ ብቻ የሚያደርግ ነው፡፡ ምዕራፍ አስር በገፅ “139” ከምዕራፍ አራት ከቀረበው መልመጃ የተለየ አቀራረብ የላቸውም፡፡ ምክንያቱም በምዕራፍ አስር በገፅ 139 የቀረበው የሰዋስው መልመጃ ተማሪዎች የተሰጡትንግሶች ወደ ስም እና ቅፅል እንዲቀይሩ ከማድረግ ውጪ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ብቃት ለማጎልበት የቋንቋውን ስርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት በተቀናጀ ሁኔታ እንዴት፣ የትና መቼ መጠቀም እንደሚገባ የሚያሳዩ ስላልሆነ ነው፡፡

በአጠቃላይ በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች የቋንቋውን ፍቺና ስርዓት አገልግሎት አቀናጅቶ ከማቅረብ አንፃር ሲታዩ በሰነድ ፍተሻ አማካኝነት የተገኘው መረጃ (69.4%) የሚሆኑ የሰዋስው መልመጃዎች የቋንቋውን ፍቺና ሥርዓት፣ አገልግሎት አቀናጅቶ ከማቅረብ አንፃር የሚሰጡት ትኩረት ዝቅተኛ እንደሆነ የሚያሳይ ሲሆን አብዛኛዎቹ የሰዋስው መልመጃዎች የቋንቋውን ፍቺና ስርዓት፣ አገልግሎት አቀናጅቶ ለማስተማር የሚሰጡት ትኩረት ዝቅተኛ መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

### 4.1.1.2 በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍት የተማሪ ተኮር አቀራረብ

በመማሪያ መፅፍት ውስጥ የተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚሰጡና የማይሰጡ እንዳሉ ለመለየት የተቻለ ሲሆን ለዚህም እንደ ማሳያ ከዚህ በታች በተናጠል ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

**ሠንጠረዥ ”መ” በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍት ተማሪ ተኮር የሰዋስው መልመጃዎች አቀራረብ**

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የማይሰጡ የሚለው ሰፊውን ሽፋን ይዞ የሚገኝ ሲሆን በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች ተማሪዎች በቋንቋው ሥርዓት ላይ ብቻ ትኩረት እንዲያደርጉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለዚህም እንደ ማሳያ የቀረበውን ሠንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡

| ተ.ቁ | በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት ሰዋስው መልመጃዎች ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት ከመስጠት አንፃር | የድግግሞሽ መጠን | መጠን |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚሰጡ | 4 | 36.4 |
| 2 | ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የማይሰጡ | 7 | 63.6 |

በሠንጠረዥ ”መ” ከቀረበው የመረጃ ውጤት እንደምንረዳው ከሆነ በመማሪያ መፅሐፉ ከቀረቡት 11 መልመጃዎች ውስጥ 4(36.4%) የሚሆኑት የሰዋስው መልመጃዎች ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚሰጡ ሲሆን 7(63.6%) የሚሆኑት የሰዋስው መልመጃዎች ደግሞ ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የማይሰጡ መሆኑን ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ በገፅ 24፣ 109 እና 156 ላይ የቀረቡትን ሶስት የሰዋስው መልመጃዎችን በአስረጅነት በመውሰድ የመረጃውን ውጤት ግልፅ በሆነ መንገድ እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

**በምዕራፍ ሁለት በገፅ “24” ላይ የቀረበውን ጥያቄ ስንመለከት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላት በነፃ ምዕላድና በጥገኛ ምዕላድ ከለያችሁ በኋላ በምሳሌው መሠረት በሠንጠረዥ ውስጥ አስፍሩ፡፡**

| ተ.ቁ | ቃል | | ነፃ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ምሳሌ | ቂመኛ | ቂም | -ኧኛ |
| 2 | ሴትነት | | | |
| 3 | ቤቶች | | | |
| 4 | ብልጠት | | | |

የሚሉ ሲሆን በምዕራፍ ስድስት በገፅ “109” ላይ የቀረበውን መልመጃ ስንመለከት ደግሞ የሚከተሉትን መነሻና መድረሻ ቅጥያዎችን በመጠቀም ቃላትን መስርቱና ዐ.ነገሮች ስሩባቸው፡፡ ምሳሌ፡- -ዎች፣ -ኦች፣ ሲ-፣ እየ-፣ ስለ፣ በ- የሚሉ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በምዕራፍ ዘጠኝ በገፅ 156 ላይ የቀረበውን ጥያቄ ቁጥር ሶስትን ስንመለከት ደግሞ በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች የሚከተሉትን (ባለቤትነትን፣ አገናዘቤ አጸፋነትን፣ ተሳቢነትን) ብዙ ቁጥርን ግለፁ፡፡

ሀ. ተናገረች ሐ. ሥራን

ለ. መፅሐፋቸውን መ. ልብሶች የሚሉ ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ጥያቄዎች እንደምንረዳው በምዕራፍ ሁለት በገፅ “24” በጥያቄ ቁጥር አንድ ላይ የቀረበውን መልመጃ ተማሪዎች በሠንጠረዥ ውስጥ የቀረቡትን ቃላት ነፃና ጥገኛ ምዕላድ እያሉ እንዲገልፁ ብቻ የሚያደርግ ሲሆን በምዕራፍ ስድስት በገፅ “109” በጥያቄ ቁጥር አንድ ላይ የቀረበው የሰዋስው መልመጃ ደግሞ ተማሪዎች -ዎች፣ -ኦች፣ ሲ-፣ እየ፣ ስለ -፣ በ- በሚሉ መነሻና መድረሻ ቅጥያዎችን በመጠቀም ዐ.ነገሮችን እንዲመሰርቱ የሚያደርግ ነው፡፡ በተጨማሪም በምዕራፍ ዘጠኝ በገፅ “156” በጥያቄ ቁጥር ሶስት ላይ የቀረበው የሰዋስው መልመጃ ደግሞ ተማሪዎች በቃላቱ ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች ባለቤትነትን፣ አገናዛቢ አፀፋነትን፣ ተሳቢነትን፣ ብዙ ቁጥርን የሚያመለክቱ ጥያቄዎችን በቋንቋው ሥርዓት ብቻ ተንተርሰው እንዲሰሩ የሚያደርግ እንጂ ተማሪዎች የተለያዩ ሀሳቦችን የመተንተን የመግለፅና የማደራጀት ክህሎታቸውን እንያዳብሩ እንዲሁም ያላቸውን ሀሳብ ከጓደኞቻቸዉ ጋር በቡድንና በጥንድ በመሆን እንዲለዋወጡ የማያደርጉ ናቸው፡፡ ይህ መረጃ ደግሞ የሚያመለክተው

በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች ምንም እንኳን ተማሪዎች እንዲሰሩ የሚያዙ በመሆኑ የሚደገፍ ቢሆንም በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች ከተማሪ ተኮር አቀራረብ አንፃር ሲታዩ ግን የአቀራረብ ችግር የሚንፀባረቅባቸው የሰዋስው መልመጃዎች እንዳሉ ነው፡፡

**ሠንጠረዥ "ሠ" በአስረኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ የተማሪ ተኮር አቀራረብ**

በአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ለተማሪ ተኮር አቀራብ ትኩረት የሚሰጡ ሚለው ከማይሰጡት ጋር በተወሰነ መልኩ ተመጣጣኝ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህንንም እንደ ማሳያ ከዚህ በታች ከቀረበው ሠንጠረዥ በቁጥርና በፐርሰንት ተለይተው ቀርበዋል፡፡

| ተ.ቁ | በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት ከመስጠት አንጻር | የድግግሞሽ መጠን | |
|---|---|---|---|
| 1 | ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚሰጡ | 6 | 46.2 |
| 2 | ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የማይሰጡ | 7 | 53.8 |

በሠንጠረዥ "ሠ" ከቀረበው መረጃ ውጤት እንደምንረዳው ከሆነ በመማሪያ መፅሀፉ ከቀረቡት 13 መልመጃዎች ውስጥ 6 ወይም (46.2%) የሚሆኑት የሰዋስው መልመጃዎች ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚሰጡ ሲሆን 7 ወይም (53.8%) የሚሆኑት የሰዋስው መልመጃዎች ደግሞ ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የማይሰጡ መሆኑን ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ በገፅ 27፣ 45፣ 61፣ 96 ላይ ቀረቡትን ከአራት የሰዋስው መልመጃዎች ውስጥ ሁለት የሰዋስው መልመጃዎችን ለአብነት እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

በምዕራፍ ሁለት በገፅ "27" ላይ የቀረበውን መልመጃ ስንመለከት በሚከተሉት ዐ.ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ሀረጎች መሪ ቃልና የሐረጎቹን አይነት በምሳሌው መሠረት ፅፋችሁ አመልክቱ፡፡

1. ትናንት የታመመው ተማሪ <u>ወደ ሆስፒታል</u> ተወሰደ፡፡
2. ወይኒቱ <u>እንደወንድሟ በጣም ጎበዝ</u> ተማሪ ናት፡፡
3. እህቱ <u>ስለመጣች ደስ</u> አለው፡፡

4. ጫልቱ <u>እንደ እህቷ ቶሎ</u> ትከፋለች፡፡

5. አያና <u>የእግር ኳስ ጫዋታ ለመመልከት ስቴዲየም</u> ገባ፡፡

የሚሉ ሲሆን በምዕራፍ ሰባት በገፅ "96" ላይ የቀረበውን መልጃ ስንመለከት ደግሞቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ቀጥተኛ ፍቺ ከመዝገባ ቃላት ፈልጋችሁ በደብተራችሁ አስፍና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. ትንቢት　　　　ሠ. ህዳሴ

ለ. ህዳሴ　　　　ረ. መባቻ…

መ. ኩርባ

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ጥያቄዎች እንደምንረዳው በምዕራፍ ሁለት በገፅ "27" የቀረበው መልመጃ ተማሪዎች ዐ.ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ሀረጎች እንዲለዩ የሚያደርግ ሲሆን በምዕራፍ ሰባት በገፅ "96" የቀረበው የሰዋስው መልመጃ ደግሞ የቃላት ቀጥተኛ ፍቺ እንዲሰጡ ከማድረግ ውጪ በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ አብዛኛውን የሰዋስው መልመጃዎች ተማሪ ተኮር አቀራረብን ያልተከተሉ በተመሳሳይ አስረኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ላይ በተወሰነ መልኩ ተማሪ ተኮር አቀራረብን ያልተከተሉ መሆናቸውን ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡

### 4.1.1.3 በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት የሂደት ተኮር አቀራረብ

ከላይ በምዕራፍ ሁለት ለማብራራት እንደተሞከረው ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ በዋናነት ከምሳሌው ተነስተው ወደ ህጉ የሚሄዱ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ከዚህ አኳያ በመማሪያ መፅሐፍቱ ውስጥ ከሂደት ተኮር የሰዋስው አቀራረብ ይልቅ የውጤት ተኮር የሰዋስው አቀራረብ ትልቅ ቦታ የሚሰጡ እንደሆነ ለመለየት ተችሏል፡፡ ለዚህም ማሳያ ሊሆን የሚችል የእያንዳንዳቸውን የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ከዚህ በታች በትንተና ቀርቧል፡፡

#### ሠንጠረዥ "ረ" በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ከሂደት ተኮር አቀራረብ አንፃር

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ለሰዋስዋዊ ህግጋት ወይም ውጤት ተኮር የሰዋስው አቀራረብ ሰፊውን ቦታ ይዞ ይገኛል፡፡ ለዚህም እንደ ማሳያ በቁጥር የተገኘውን ውጤት ወደ ፐርሰንት በመቀየር ከዚህ በታች በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብን በማድረግ ከማቅረብ አንፃር | የድግግሞሽ መጠን | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ገፅ | በቁጥር | % |
| 1 | ውጤት ተኮር ሰዋስው ትምህርት አቀራረብ | 26፣70፣86፣125፣128፣ | 9 | 81.8 |
| 2 | ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ | 141፣143 | 2 | 18.2 |

በሠንጠረዥ "ረ" የቀረበው ውጤት እንደሚያሳየው ከሆነ ደግሞ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች ከሂደት ተኮር የሰዋስው አቀራረብ ይልቅ ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብን መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ እንደሆነ ነው። ምክንያቱም በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ "11" የሰዋስው መልመጃዎች ውስጥ 9 ወይም (81.8%) የሚሆኑት የሰዋስው መልመጃዎች ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ ሲሆን 2 ወይም (18.2%) የሚሆኑት የሰዋስው መልመጃዎች ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብን መሠረት በማድረግ ተዘጋጁ ስለሆነ ነው። ይህንን ሀሳብ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ በገፅ 141 እና 143 ላይ የቀረቡትን ሰዋስው መልመጃዎችን በአስረጅነት በመውሰድ የመረጃውን ውጤት ግልፅ በሆነ መንገድ እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል።

በምዕራፍ ስምንት በገፅ "141" ላይ የቀረበውን ጥያቄ ቁጥር ሁለትን ስንመለከት በሚከተሉት ቃላት ውስጥ አምስት ቅፅላዊ ሀረጎችን በመመስረት ዐ.ነገር ስሩባቸውና ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

ምሳሌ፡- የልጅ አዋቂ - የሕፃን ብልጥ - የተማሪ ብልህ

- አዋቂ - የወጣት
- አዋኪ - ብልህ
- ብልጥ - ደግ

የሚሉ ናቸው። በምዕራፍ ስምንት በገፅ 143 የቀረበውን ጥያቄ ቁጥር ሶስትን ስንመለከት ደግሞ የሚከተሉት ዐ.ነገሮች እያንዳንዳቸውን በስማዊ ሀረግና በግሳዊ ሀረግ ከፋፍላችሁ በሠንጠረዥ በማቅረብ ዐ.ነገሮቹን በስማዊ ሀረግና በግሳዊ ሀረግ ለመክፈል ምክንያት የሆናችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርባችሁ ተነጋገሩበት።

1. ሁለት ሙሉ ልብስ እንድታሰፋ ጓደኛዋ ገንዘብ ሰጣት፡፡
2. ታናሽ እህቴ ከቤተሰቦቻችን ሁሉ የተለየች ባለሙያ ናት፡፡
3. ንፅህናው ያለተጠበቀ ምግብ የበላው ተማሪ ታመመ፡፡

የሚሉ ሲሆን በምዕራፍ ስምንት በገፅ 143 ላይ ቀረበውን ጥያቄ ቁጥር አራትን ስንመለከት ደግሞ በሚከተሉት ዐ.ነገሮች ውስጥ ተራና ውስብስብ የሆኑትን በመለየት ተራ እና ውስብስብ ያላችሁባቸውን ምክንያቶች ለይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

1. ልጁ ዛሬ ጥዋት ብዙ ጥያቄዎችን አቀረበልኝ፡፡
2. ጨዋታውን ፊት ለፊት በማየቴ ደስ አለኝ፡፡
3. ግርማ ሆስፒታል ሄዶ ወንድሙን ጠየቀ፡፡
4. እንግዳው ሰውዬ ዛሬ ጥዋት ወደ ሀገሩ ተመለሰ፡፡ የሚሉ ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ጥያቄዎች እንደምንረዳው ከሆነ የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች ከሂደት ተኮር የሰዋስው አቀራረብ ይልቅ ውጤት ተኮር የሰዋስው አቀራረብን መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ እንደሆነ ነው፡፡

ምክንያቱም በምዕራፍ ስምንት በገፅ 141 ላይ ከተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ አምስቱን በመምረጥ ቅፅላዊ ሀረጎችን እንዲመሠርቱ የሚያደርግ ሲሆን በገፅ 143 በጥያቄ ቁጥር ሶስት ላይ እያንዳንዳቸውን ዐ.ነገሮች በስማዊ ሀረግና በግሳዊ ሀረግ ለመክፈል ምክንያት ሆናቸውን ጉዳይ ለክፍል ጓደኞቻቸው በማቅረብ እንዲነጋገሩበት የሚያደርግ በመሆኑ ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራብን ወይም ከህጉ በመነሳት ወደ ምሳሌው የሚሄደውን የሰዋስው ትምህርት አቀራረብን መሠረት ያደረገ ስለሆነ ነው፡፡

## ሠንጠረዥ "ሰ" በአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የሂደት ተኮር አቀራረብ አንፃር

በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከሂደት ተኮር የሰዋስው አቀራረብ ይልቅ ለውጤት ተኮር የሰዋስው አቀራረብ ሰፊ ቦታ ተሰጠው መሆኑን ከዚህ በታች ከሠንጠረዡ መረዳት ይቻላል፡፡

| ተ.ቁ | በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች ሂደት ተኮር አቀራረብን በማድረግ ከማቅረብ አንፃር | የድግግሞሽ መጠን | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ገፅ | በቁጥር | % |
| 1 | ውጤት ተኮር ሰዋስው ትምህርት አቀራረብ | 72፣83፣86፣141፣156፣ | 11 | 84.6 |
| 2 | ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ | 85፣160 | 2 | 15.4 |
| | አጠቃላይ ድምር | | | |

ከላይ በምዕራፍ ሁለት ለማብራራት እንደተሞከረው ሂደት ተኮር ሰዋስው ትምህርት አቀራረብ በዋናነት ከምሳሌው ተነስቶ ወደ ህጉ ወይም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚያቀርብ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ከዚህ አንጻር በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብን በተከተለ መልኩ የተቀመጡ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች እንዳሉ ለመለየት ተችሏል፡፡ ለዚህም ማሳያ ሊሆን የሚችል ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**በገፅ 72 ከዚህ በታች በሠንጠረዥ የተዘረዘሩ ሀረጋት በመለየት በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ተግባራቸውን ግለፁ፡፡**

| ተ.ቁ | ግሳዊ ሀረግ | ስማዊ ሀረግ | ቅፅላዊ ሀረግ | ተ.ግሳዊ ሀረግ | መስተዋድዳዊ ሀረግ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የማይቻል ነገር የለም | የተማሩ ሰው | ምንም የማይቻል | አሁኑኑ ቶሎ | ከአእምሮ ውስጥ |
| 2 | | | | | |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ እንደሚያመለክተው ተማሪዎቹ በተሰጣቸው ሰዋስዋዊ መዋቅር የተለያዩ ቃላት በውስጣቸው የያዙትን የሀረጎችን ዓይነት እንዲለዩ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህም በቋንቋው መዋቅር ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ የሰዋስው ትምህርቱ ውጤት ተኮር አቀራረብ እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በዘጠነኛና በአሥረኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብን መሠረት ከማድረግ አንፃር ሲታይ በሠነድ ፍተሻ አማካኝነት የተገኘው መረጃ (15.4%) የሚሆኑት የሰዋስው መልመጃዎች ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብን መሠረት በማድረግ እንዳልተዘጋጁ ከሠነድ ፍተሻው ለመረዳት ተችሏል፡፡

#### 4.1.1.4 በዘጠነኛና በአሥረኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍት ውስጥ እውናዊነት ተላብሶ ከማቅረብ አንጻር

በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ተግባራት በሚቀርቡበት ጊዜ እውናዊ ለሆኑ ተግባራት ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም እውናዊ የሆኑ የሰዋስው ትምህርት ተግባራትን በመጠቀም የቋንቋ ትምህርት የምናስተምር ከሆነ ተማሪዎች በቋንቋ የመግባባት ክህሎታቸውን በእውኑ አለም ላይ ያለውን ክፍል ውስጥ በበለጠ ሁኔታ እንዲጠቀሙበት ሊያደርጋቸው የሚችል መሆኑን ከላይ በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል፡፡ ነገር ግን መማሪያ መፅሐፍቱ ይህንን መሠረት አድርገው ያልቀረቡ መሆኑን ከዚህ በታች ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት ይቻላል፡፡

**ሠንጠረዥ ”ሸ” በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የእውናዊነት አቀራረብ**

በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ እውናዊነትን ያልተላበሱ ሰፊውን ቦታ የያዙ ሲሆን ለዚህም ማሳያ ሊሆን የሚችል ከዚህ በታች ከቀረበው ሠንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡

| ተ.ቁ | በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች እውናዊነትን ተላብሶ ከመቅረብ አንፃር | የድግግሞሽ መጠን | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ገፅ | በቁጥር | % |
| 1 | እውናዊነትን ያልተላበሱ | | 10 | 90.9 |
| 2 | እውናዊነትን የተላበሱ | | 1 | 9.1 |

በሠንጠረዥ ”ሸ” መማሪያ መጽሐፍ ከቀረበው መረጃ እንደምንረዳው ከሆነ ደግሞ በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከቀረቡት አሥራ አንድ መልመጃዎች ውስጥ 10 ወይም (90.9%) የሚሆኑ የሰዋስው መልመጃዎች እውናዊነትን መሠረት በማድረግ ያልተዘጋጁ ሲሆን 1 ወይም (9.1%) የሚሆነው የሰዋስው መልመጃ ደግሞ አውናዊነትን መሠረት በማድረግ የቀረበ እንደሆነ ነው፡፡ ይህን ሀሳብ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ በገፅ 72፣ 141፣ እና 143 ላይ የቀረቡትን ሶስት የሰዋስው መልመጃዎችን በአስረጅነት በመውሰድ የመረጃውን ውጤት እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ ምዕራፍ አራት በገፅ “72” ላይ የቀረበውን ጥያቄ ቁጥር ስድስትን ስንመለከት ከላይ በቀረበው መግለጫና ምሳሌ መሠረት በዐ.ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ሀረጎች ከየትኛው የሀረግ ዓይነት እንደሚመደቡ (የሀረግ አይነታቸውን) ግለፁ፡፡

1. ሰፊ ብርድ ልብስ አለው፡፡
2. ዘገየ በጣም ታታሪ ሰው ነው፡፡
3. ደራሲው ጥሩ ፅሑፍ ፃፈ፡፡
4. የወንድሜ ልጅ ከክፍሉ አንደኛ ወጣ፡፡
5. አበበ ክፉኛ ታሟል፡፡
6. ያልሰራ ሰው ሁልጊዜ ይራባል፡፡

የሚሉ ሲሆን በምዕራፍ ስምንት በገፅ 141 ላይ የቀረበውን ጥያቄ ቁጥር አንድን ስንመለከት ደግሞ ከሚከተሉት ቃላት አምስቱን ምረጡና ስማዊ ሀረግ መስርቱ፤ ከዚያም ዐ.ነገር ስሩባቸው፡፡

ምሳሌ፡- ረዥም ገመድ፣ የእግር መንገድ፣ የፈተና ወረቀት

- ረዥም - ትልቅ - ቀይ
- መንገድ - ሰው - ብዕር
- ወረቀት - አካፋ የሚሉ ናቸው፡፡

**ሠንጠረዥ "ቀ" በአሥረኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ከእውናዊነት አንፃር**

በአስረኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ እውናዊነትን ያልተላበሰ ከፍተኛውን ቁጥር ይዞ ይገኛል፡፡ ይህንንም ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ከዚህ በታች የቀረበውን ሠንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡

| ተ.ቁ | በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች እውናዊነትን ተላብሶ ከመቅረብ አንፃር | የድግግሞሽ መጠን | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ገፅ | በቁጥር | % |
| 1 | እውናዊነትን የተላበሱ | 85፣160 | 11 | 84.6 |
| 2 | እውናዊነትን ያልተላበሱ | | 2 | 15.4 |

በተመሳሳይ የአስረኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ላይ በገፅ 72 ጥያቄ ቁጥር ሁለት ቀጥሎ በቀረበው ምሳሌ መሠረት ከተሰጣችሁ ውስብስብ ዐ.ነገሮች ተራ ዐ.ነገሮችን መስርቱ፡፡

1. በፍጥነት ነዳ፡፡
2. ወደ ሥራ ሄደ፡፡
3. ከጭነት መኪና ጋር ተጋጨ፡፡
4. ክፉኛ ቆሰለ፡፡

የሚሉ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም በጥያቄ ቁጥር አንድ ላይ የሀረጋት ምሥረታ ህግጋትን በመመርኮዝ " ምንም የማይቻል ነገር የለም " በሚለው ፅሑፍ ውስጥ የሚገኙት ሀረጋትን በተሰጠው ሠንጠረዥ ውስጥ በአይነታቸው መድቧቸው፡፡

| <u>ግሳዊ ሀረግ</u> | <u>ስማዊ ሀረግ</u> | <u>ተ.ግ.ሀረግ</u> | <u>መስተዋድዳዊ ሀረግ</u> |
|---|---|---|---|
| **ምሳሌ፡-**የማይቻል ነገር የለም | የተማሩ ሰው | አሁኑኑ ቶሎ | አእምሮየ ውስጥ |

ሀ. _________

ለ. _________

ሐ. _________

መ. _________

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ጥያቄዎች እንደምንረዳው ከሆነ በዘጠነኛና በአሥረኛ ክፍል የቀረቡት አብዛኛው የሰዋስው መልመጃዎች እውናዊነትን መሠረት በማድረግ ያልተዘጋጁ እንደሆኑ ነው፡፡ ምክንያቱም በዘጠነኛ ክፍል በምዕራፍ አራት በገፅ 141 እና 143 በጥያቄ ቁጥር አንድና ሶስት ላይ እና በአስረኛ ክፍል በገፅ "72" ላይ የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች እውናዊ ባልሆነ አውድ ውስጥ እንደሚመደቡ፣ የሀረግ አይነታቸውን ብቻ እንዲገልፁ ከተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ ስማዊ ሀረግ እንዲመሠርቱ ከዚያም ስማዊ ሀረጉን ለመክፈል ምክንያት የሆናቸውን ነገሮች ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ የሚያደርጉ ስለሆነ ነው፡፡

በአጠቃላይ በዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ አብዛኛዎቹ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ተማሪዎች የቋንቋውን ሥርዓት ለይተው እንዲያውቁ ከማድረግ ውጪ ታላሚውን ቋንቋ በመጠቀም በእውኑ ዓለም ላይ በትክክል እንዲግባቡበት የሚሰጡት ትኩረት ዝቅተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም አብዛኛዎቹ የሰዋስው መልመጃዎች አቀራረባቸው የቋንቋውን ሥርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት አቀናጅተው የሚያስተምሩ፣ እውናዊነት የጎደላቸው ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የማይሰጡና ከምሳሌ ተነስተው ወደ ህጉ የማይሄዱ ስለሆነ ተማሪዎች በጥንድና በቡድን በመሆን እንዲወያዩ ወይም የተለያዩ የሰዋስው መልመጃዎችን እንዲሰሩ፣ ሀሳባቸውን፣ ስሜታቸውንና አመለካከታቸውን እንዲለዋውጡ እንዲሁም የተማሪዎችን ትብብራዊ መማርና ተግባቦታዊ ብቃት የማያጎለብቱ ከመሆኑም በላይ ለተማሪዎች የተለያዩ መዋቅሮችን እንዴት፣ የትና፣ መቼ መጠቀም እንዳለባቸውና በዲስኩር ጊዜ የትኛው የሰዋስው

መዋቅር መቅደምና መከተል እንዳለበት የማያሳውቁ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ አቀራረብ የሚታየው ደግሞ ብዙውን ጊዜ ጎልቶ የሚታየው በጥንታዊ የሰዋስው ላይ ነው፡፡
ምክንያቱም የጥንታዊ የሰዋስው አቀራረብ ይዘቶች የሚደራጁት ሥነ-ድምፀ ልሳናዊ፣ ቃላዊና ዐ.ነገራዊ መዋቅር ቅርፆችን መሠረት በማድረግ በመሆኑ የሰዋስው መልመጃዎች የሚቀርቡት ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ተግባራትን የቋንቋውን ሥርዓት መሠረት በማድረግ በመተካካትና በመለዋወጥ እንዲሠሩ በማድረግ ስለሆነ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት ተማሪዎች እያንዳንዱን የቋንቋ ጡቦች ነጣጥለው የሚማሩ ከሆነ በታላሚው ቋንቋ የመግባባት ዕድላቸው ከፍተኛ ይሆናል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡

### 4.1.2 ዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀት

በመማሪያ መፅሐፍቱ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ከአደረጃጀት አንፃር የመገምገሚያ መስፈርት የሆኑትን ከተከታታይነት፣ ከተለጣጣቂነትና ከውህደት አንፃር ከዚህ በታች በተናጠል እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

#### 4.1.2.1 የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀት ከተከታታይነት አንፃር

በምዕራፍ ሁለት በተዛማጅ ፅሑፎች ቅኝት እንደተመለከተው ተከታታይነት የሚለው የመልመጃዎች አደረጃጀት መስፈርት የሚያመለክተው የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ሲደራጁ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከግልፅ ወደ ውስብስብ በሂደት የሚመጣውን ክትትሎሽ የሚያሳዩ እንዲሆኑ በአንድ ምዕራፍ የቀረቡት በሌላው ምዕራፍ ሲደገሙ በመልመጃው ውስጥ ያለውን ቀጣይ ክፍል በማስተካከል የሚደራጁበት ሁኔታ መፍጠርን እንዲሁም በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች መልመጃዎች በቀጣይ ለሚገኙ ተማሪዎች ተመሳሳይ የትምህርት ዓይነት ወይም መልመጃ እንደየክፍል ደረጃቸው መጥኖ ማቅረብን ያካትታል፡፡ ለዚህም በዘጠነኛ ክፍል የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች በቀጣይ በአሥረኛ ክፍል ከቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች ጋር የአካቶና የጥልቀት የአቀራረብ አግባብ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በዘጠነኛና በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መጸሀፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው መልመጃዎች ተከታታይነት ባለው መልኩ ማለትም የአሥረኛ ክፍል፣ ከዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ተመስርቶ በተዋረድ የማቅረቡ ሁኔታ ሲታይ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች ተመሳሳይ የትምህርት መልመጃ ያላቸው ሰዋስዋዊ መልመጃዎች ቀርበው እናገኛቸዋለን፡፡ የአቀራረቡም ሁኔታ የተማሪዎችን ደረጃ ባገናዘበ ሁኔታ በመማሪያ መፃህፍቱ ለማደራጀት ተሞክሯል፡፡

ለዚህም እንደ ማሳያ በሁለቱ የክፍል ደረጃዎች የቀረቡ ተመሳሳይ የትምህርት መልመጃዎችን በማንሳት የመልመጃዎችን ተከታታይነት አቀራረብ ስንመለከት፡-

- የምዕላድ መልመጃዎች
- የእማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች መልመጃዎች
- የሀረግ መልመጃዎች
- የዐረፍተ ነገር የሚሉ ቀጣይነት ያላቸው አደረጃጀቶች እናገኛለን፡፡

ከላይ ለማሳያነት የተጠቀሱት የምዕላድ፣ የሀረግና የእማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍችን የተመለከቱ የትምህርት መልመጃዎች በዘጠነኛና በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ውስጥ በቀጣይነት የቀረቡ ናቸው፡፡ እነዚህ መልመጃዎች በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በዘጠነኛና በአሥረኛ ክፍል የሚገኙ ቢሆንም፣ ከአቀራረብ አንፃር የተለያዩና በስፋትና በጥልቀት ልዩ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

<u>**ለምሳሌ**</u>፡- በአስረኛ ክፍል የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍችን በተመለከተ በገጽ 45 ላይ አጭር ማብራሪያ ከሰጠ በኋላ በሰንጠረዡ የቀረቡትን ቃላት እንዲለዩ ይጠይቃል፡፡

ከዚህም መረዳት የሚቻለው በአሥረኛ ክፍል ውስጥ የቀረበው የሰዋስው መልመጃ ከቀጣይነት አንፃር በተገቢው ሁኔታ ተደራጅቶ መቅረቡን ነው፡፡

ይህን ሀሳብ የበለጠ የሚያጠነክርልን ሌላው አብነት ደግሞ በአስረኛ ክፍል የምዕላድ ዓይነት በሚለው የቀረበው መልመጃ ውስጥ ገፅ 125 ላይ…ቅጥያ ምዕላድ እየመረጣችሁ ለነፃ ምዕላዶች ተስማሚ የሚሆኑትን በመምረጥ በመቀጠል ቃላትን እንዲመሠርቱ የሚጠይቅ ሲሆን፣ በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተመሳሳይ በገፅ 25 ላይ ስለ ምዕላድ ምንነት በምንባብ ደረጃ ከተብራራ በኋላ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ በቃልና በምዕላድ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በማብራራት ቃላት እንዲመሠርቱ ይጠይቃል፡፡ ከዚህም መረዳ የሚቻለው በአስረኛ ክፍል ውስጥ የቀረበው የሰዋስው መልመጃ ከቀጣይነት አንፃር በተገቢው ሁኔታ ተደራጅቶ መቅረብ እንደቻለ ነው፡፡

ሌላው አብነት በዘጠነኛ ክፍል ዐረፍተ ነገር በሚል አርዕስት በገፅ 72 የዐረፍተ ነገር የማስሪያ አንቀፅ የባለቤት ክፍል በሚል ማብራሪያ የቀረበ ሲሆን የተዘረዘሩ ዐረፍተ ነገሮች ላይ ለመለየት ምክንያት የሆናችሁን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ሲሆን፣ በአሥረኛ ክፍል

መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተመሳሳይ በገፅ 113 የዐረፍተ ነገር አይነትን አብነቶች በማቅረብ በገፅ 114 የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮችን ለይተው አቅረቡ በሚል የቀረበ ነው፡፡

በአስረኛ ክፍል የሀረግአይነቶችን በተመለከተ በገፅ 26 የሀረግ አመሰራረት በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን የተዘረዘሪ የሀረግ አይነቶችን ስያሜ እንዲያሰፍሩ የሚጠይቅ ሲሆን በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ በተመሳሳይ በገፅ 141 የሀረግን ምንነትና አይነቶች በምሳሌ ካሳየ በኂላ የተሰወረባቸውን ሀረግ ከየትኛው የሀረግ አይነት እንደሚመድቡ ግለፁ በሚል የቀረበ ሲሆን ይህም ቀለል ባሉ ሀረጋት ተማሪዎች እንዲረዱት የሚያስችል ነው፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው በአስረኛ ክፍል ውስጥ የቀረበው የሰዋስው መልመጃ ከቀጣይነት አንፃር በተገቢው ሁኔታ ተደራጅቶ መቅረብ እንደቻለ ነው፡፡

ከላይ የቀረቡትን ለምሳሌ አነሳን እንጂ ሌሎች በርካታ መልመጃዎች በአግባቡ ተከታታይነታቸውን ጠብቀው ቀርበዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ በተለየ መልኩ በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች በአሥረኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ቅስጥ መካተት አለመቻላቸው በድክመት ሊነሳ የሚችል ነው፡፡ ይኸውም የቃል ክፍሎችና የቃል ክፍሎች ሙያ፣ የሀረግ አመሠራረት ሰፋ ባለ እና ለየት ባለ መልኩ መቅረብ ሲገባቸው ያልተካተቱ ናቸው፡፡ በተጨማሪም አገባባዊ ፍች፣ አያያዥ መሽጋገሪያ ቃላት/ሀረጋት፣ የዐረፍተ ነገር ስልቶች በቃል ክፍሎች ሀረጋትን መመስረት፣ ተራና ውስብስብ ዐረፍተ ነገሮችን እንዲሁም ሀረጋትን መመስረት የሚሉት መልመጃዎች በአስረኛ ክፍል ውስጥ ተካተው በዘጠነኛ ክፍል ውስጥ ያልተካተቱ ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ከዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ አንፃር ሲታይ በውስጡ ያካተቷቸው የሰዋስው መልመጃዎች ቀጣይነት ባለው መልኩ የተደራጀበት መሆኑን ያሳያል፡፡ እነዚህንም ጉዳዮች ከሚከተሉት ሠንጠረዦች መመልከት ይቻላል፡፡

**ሠንጠረዥ “በ” በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች ከተከታታይነት አንፃር**

| ተ.ቁ | በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከተከታታይነት አንፃር ቀረቡ መልመጃዎች | በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከተከታታይነት አንፃር ቀረቡ መልመጃዎች |
|---|---|---|
| 1 | ነፃ እና ጥገኛ ምዕላድ | ነፃና ጥገኛ ምዕላድ |
| 2 | እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ | የዐ.ነገር ክፍሎች |
| 3 | የቃል ክፍሎች | ከግስ ስምና ቅፅልን መመስረት |
| 4 | ዐ.ነገሮችን በአይነት መመደብ | የዐ.ነገር ስልቶችን መለየት |
| 5 | የሀረግ ዓይነቶች | ሀረጋትን መመስረት |
| 6 | የቃል ክፍሎች ሙያ | ተራና ውስብስብ ዐ.ነገሮችን መለየት |

**ሠንጠረዥ “ተ” በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል መርሀ ትምህርት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች ከተከታታይነት አንፃር**

በዘጠነኛና አስረኛ ክፍ የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ያላቸውን ተከታታይነት ከዚህ በታች በሠንጠረዥ ”ተ” በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

| ተ.ቁ | በዘጠነኛክፍል መርሀ ትምህርት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች | በአስረኛ ክፍል መርሀ ትምህርት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች |
|---|---|---|
| 1 | ነፃና ጥገኛ ምዕላድ | በቃል ክፍሎች ሀረጋትን መመስረት |
| 2 | እማሬያዊና ፍካሬያዊዎች | አያያዥና መሸጋገሪ ቃላት/ሀረጋት |
| 3 | የቃል ክፍሎች | የዐረፍተ ነገር ክፍሎች |
| 4 | ቃላትንና ሀረጋትን ማዋቀር | ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች |
| 5 | ዐረፍተ ነገሮችን በአይነት መመደብ | ከግስ ስምና ቅፅል መመስረት |
| 6 | አውድን ተጠቅሞ ተቃራኒ ፍች መስጠት | የዐረፍተ ነገር ስልቶች |
| 7 | ቃላትን በምንባብ ውስጥ ያላቸውን ፍች መለየት | ሀረጋትን መመስረት |
| 8 | የሀረግ አይነቶች | ተራ እና ውስብስብ ዐረፍተ ነገሮችን መመስረት |
| 9 | የዐረፍተ ነገር ክፍሎች | ምዕላድን መተንተን |
| 10 | የቃል ክፍሎች ሙያ<br>የቃላት መጥበቅና መላላት | በቃላት ውስጥ የድምፅ መጥበቅና መላላት፣ መርዘምና ማጠር |

ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል በርሀ ትምህርቶች የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች በሙሉ ለደረጃው ይመጥናሉ ተብለው በተዘጋጁት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ አብዛኛዎቹ የተደጋገሙ ቀጣይነት ባለው መል ጥቂቶች ደግሞ ሳይደገሙ ቀርበዋል፡፡ ከቀጣይነት አንፃር መማሪያ መፃህፍቱና መርሀ ትምህርቱ ጥብቅ ትስስር እንዳላቸው ማየት ተችሏል፡፡ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች በሙሉ በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ተካተው ይገኛሉ፡፡ በዚህ መሠረት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍትና መርሃ ትምህርቱ ስምምነት ያላቸው ናቸው ለማለት ያስደፍራል፡፡ አሁንም በማሳያነት በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ለምሳሌ በዘጠነኛ ክፍል መርሀ ትምህርት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ተካተው የቀረቡ ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡- በመርሃ ትምህርቱ ቃል ከየትኛው የቃል ክፍል እንደሚመደብ መምህራን ገለፃ አድርገው በዘጠነኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ውስጥ የሚከተሉት ቃላት ወርበው እናገኛለን፡፡

ገደለ፣ መታ… ከሚሉ ግሶች ግሶችን መስርታችሁ አሳዩ፡፡ ለምሳሌ በተነ፣ ተበተነ፣ አስበተነ

-ኦች፣ ሲ፣ የሚሉ መነሻና መድረሻ ቅጥያዎችን በመጠቀም ቃላትን መስርቱና ዐረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

ግንባታ፣ ልማት፣… በሚሉ ቃላት ዐረፍተ ነገር መስርቱና በዐረፍተ ነገር ውስጥ የቃሉን ሙያ ባለቤት፣ ተሳቢ እያላችሁ ግለፁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዘጠነኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎችን ስናይ በመርሃ ትምህርቱ ከተካተቱት መካከል፤

ለምሳሌ፡- በቃልና በምዕላድ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ገልፀው ስነቃሎች፣ ለበሰችሁ… የሚሉትን ቃላት ቃሉን በምዕላድ ተንትናችሁ ቅጥያ ምዕላዱንና ተግባሩን ግለጹ፡፡

ለምሳሌ፡- “ ታዬ ጊደሩን ሸጠ ወይፈን ገዛ፡፡ ” የሚሉትን ዐረፍተ ነገር ሰዋስዋዊ ስህተት ከለያችሁ በኋላ አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡

ለምሳሌ፡- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ አስቀምጡ፡፡

ቋንጣ… “አየለ መኪና ገዛ፡፡”

ሌላው በአስረኛ ክፍል በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት አላማዎችና መልመጃዎች ትስስራቸው በአብዛኛው ችግር የሌለበትና የጠበቀ መሆኑን ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት ይቻላል፡፡

ለአብነት በአስረኛ ክፍል የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱ ስዋስው ትምህርቶች ነጻና ጥገኛ ምዕላድ፣ አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት /ሀረጋት/ ተራ እና ውስብስብ ዐረፍተ ነገር፣ የቃል ክፍሎችና ሀረጋት ምስረታ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ተካተው የቀረቡ ናቸው፡፡

ለአብነት በአስረኛ ክፍል የቀረቡ ሰዋስው ስናይ በበቂ ምዕላድ ላይ የተጨመሩ ቅጥያዎችን ተግባር ገልጸው በተለያዩ የዐ.ነገር ስልቶች ዐ.ነገሮች ትፅፋላችሁ ነጻና ጥገኛ ምዕላዶችን በማቀናጀት ቃል እንዲመሠርቱ ያዝዛል፡፡

ሀተታዊ፣ ትዕዛዛዊና ጥያቄያዊ ዐረፍተ ነገሮችን መስርተው ለክፍሉ በንባብ አሰሙ፡፡

ኣት፣ ኤ… የሚሉ ጥገኛ ምዕላዶችን ግብ፣ ጦስ… በሚሉ ነፃ ምዕላዶች ተስማሚ የሚሆኑን በመቀጠል ቃላትን መርስቱ፡፡

ላምሽ፣ ወንድሙ… ከሚሉ ቃላት ውስጥ ነፃና ጥገኛ ምዕላዱን ከለያችሁ በኋላ የቅጥያ ምዕላዱን አገልግሎት አንራሩ፡፡

ውልድ፣ ክስር… ከሚሉ ግሶች ለምን ዘረፈ፣ በላ… ከሚሉ ግሶች ደግሞ ቅፅልን መስርቱ በቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ዐረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡

ተቸ፣ ነፈገ… ለሚሉ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ከሰጣችሁ በኋላ ዐረፍተ ነገር ሰርታችሁ እንዲታሳዩ የሚሉ ትዕዛዞችን እናገኛለን፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው በአስረኛ ክፍል ውስጥ የቀረበው የሰዋስው ይዘት ከቀጣይነት አንፃር በተገቢው ሁኔታ ተደራጅቶ መቅረብ እንደተቻለ ነው፡፡ መልመጃዎች በቀደመ እውቀታቸው ወይም ዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ትምህርት በተማሩት የሰዋስው መልመጃ ያልተካተቱ ቢሆኑም መነሻ ሀሳቡን ያለቀቀ ከመሆኑ አንፃር ትምህርቱ በመልመጃነት ቀርቦ መማራቸው ተገቢ ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን በዘጠነኛ ክፍል በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ውስጥ የቀረቡ አብዛኛዎቹ የሰዋስው መልመጃዎች በአስረኛ ክፍል

ውስጥ መካተት ሁሉም አለመቻላቸው እንደ ድክመት ሊነሳ የሚችል ነው፡፡ ይኸውም፣ በቃል ክፍሎች ሀረጋትን መመስረት የሚሉት ይዘቶች በአስረኛ ክፍል ውስጥ ተካተው በተለየ አቀራረብ መቅረብ ሲገባቸው ያልተካተቱ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርቱ መልመጃዎች አደረጃጀት ካላቸው ትስስር እንዲሁም ይዘቶች በመማሪያ መፅሐፉ አላማውን ለማስተግበር የሚያስችና ተገቢ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

### 4.1.2.2 የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀት ከተለጣጣቂነት አንፃር

ሌላው የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀት ስፋትና ጥልቀት በተለያየ መንገድ በማደራጀት የትምህርቱ መልመጃዎች በአንድ የክፍል ደረጃ ላይ በተደጋጋሚ ማቅረብ እና መልመጃውን በጥልቀት እንዲረዱት ማስቻልና ተመሳሳይ የሆኑ የትምህርት መልመጃዎችን በአንድ የክፍል ደረጃ ላይ በተለያየ አቀራረብ በተደጋጋሚ በተለያዩ ምዕራፎች የቀረቡበትን ሁኔታ በመዳሰስ ቀርቧል፡፡

እያንዳንዳቸውን የትምህርት ክፍሎች ለይተን ሲናይ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀት በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍ ውስጥ ያለውን ሂደት ተለጣጣቂነት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ ”ቸ” የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው መልመጃዎች ድግግሞሽ የሚያሳይ ሠንጠረዥ**

በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው መልመጃዎች ከተለጣጣቂነት አንፃር የሚያመለክቱ መልመጃዎች ከዚህ በታች ከሠንጠረዡ መመልከት ይቻላል፡፡

| አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍ ውስጥ የሰዋስው መልመጃዎች | የድግግሞሽ መጠን | | |
|---|---|---|---|
| | ገጽ | በቁጥር | በ% |
| ነፃና ጥገኛ ምዕላድ | 24፣109 | 2 | 18.1 |
| የቃል ክፍል | 69፣128፣155 | 3 | 27.2 |
| የሀረግ ዓይነቶች | 72፣141 | 2 | 18.1 |
| የዐ.ነገር ክፍሎችን መለየት እና ሀተጎችን ተጠቅሞ ዐ.ነገር መመሥረት | 86፣143 | 2 | 18.1 |
| እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች | 67 | 1 | 9.09 |
| የቃላት መጥበቅና መላላት | 175 | 1 | 9.09 |
| | | 11 | 100 |

ከላይ ሰንጠረዥ "ቸ" የሚያመለክተው የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው መልመጃዎች ለምን ያህል ጊዜ ተደጋግመው የቀረቡ ሲሆን ከድግግሞሽ አንጻር ሶስት ሰዋስዋዊ መልመጃዎች ማለትም ነፃና ጥገኛ ምዕላድ፣ የሀረግ ዓይነቶችና የዐ.ነገር ክፍሎችን መለየትና ሀረጎችን ተጠቅሞ ዐ.ነገር መመስረት የሚሉት እያንዳንዳቸው ለሁለት ጊዜ (18.1%) የተደጋገሙ ሲሆን የቃል ክፍሎችን መለየት ለሶስት ጊዜ (27.2%) ሌሎች የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች፣ በቃል ውስጥ የሚጠብቁና የሚላሉ (የሚረዝሙና የሚጠብቁ) ድምፆች እያንዳንዳቸው ለአንድ ጊዜ (9.05%) ተደጋግመው ቀርበዋል፡፡ በቀረቡት አሥራ አንድ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ውስጥ አራቱ ከሁለት እስከ ሶስ ጊዜ በድግግሞሽ የቀረቡ ሲሆን ሌሎች ሁለት መልመጃዎች ደግሞ ለአንድ ጊዜ ብቻ ቀርበዋል፡፡ በጥቅሉ 81.8% ያህል መልመጃ ድግግሞሽ እንዳለ መረዳት ይቻላል፡፡

ከመልመጃ ድግግሞሽ መረጃ በመነሳት የነፃና የጥገኛ ምዕላድን መልመጃ ተለጣጣቂነት ስናይ በምዕራፍ 2 ገፅ 24 በቀረበው ምዕላድ ምንድን ነው በሚለው ገለፃ መሠረት የዐ.ነገሮቹን ሰዋስዋዊ ስህተት ከዚህ የቁጥር፣ የፆታ፣ የመደብ በማለት ከለያቸው በኋላ ዐ.ነገሮቹን አስተካክለው እንዲያቀርቡ ያደርጋል፡፡ በምዕራፍ ስድስት ገፅ 109 ትዕዛዝ ሶስት ላይ የሚከተሉትን በነፃና በጥገኛ ምዕላድ ክፍፍሉ፣ ሙከራችሁንም ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማቅረብ እንዲነጋገሩበትና አንድ ምሳሌ በመስጠት ትዕዛዙን መሠረት በማድረግ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ነፃና ጥገኛ ምዕላዱን ለይተው እንዲገልፁ ያዝዛል፡፡ ለአብነት፡- ጥገኛ ምዕላድ -ኦች፣ ...ነፃ ምዕላድ ሰው... ተሰጥተዋል፡፡

የመልመጃዎች አደረጃጀት ድግግሞሹን ከላይ ከቀረበው ማብራሪያ የምንረዳው በመጀመሪያው ምዕራፍ ሁለት ገፅ 24 ላይ የቀረበው በምዕራፍ ስድስት ገጽ 109 ከቀረበው ጋር ያለው ተለጣጣቂነት ተገቢ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያው ተግባር የምዕላድን ምንነት በማስገንዘብ የቀረቡትን ዐ.ነገሮች ሰዋስዋዊ ስህተት እንዲለዩ በማድረግ ካለማመደ በኋላ በቀጣይ ገፅ 109 ላይ በቀረበው ተግባር ደግሞ በቃላት ውስጥ ያሉትን ጥገኛ ምዕላድ ተንትነው የጥገኛ ምዕላዱን ተግባር እንዲገልፀው መደረጉ መልመጃው ደረጃ በደረጃ እያደገና ከቀላል ወደ ከባድ ተከታትሎ የተደራጀ መሆኑን ያሳያል፡፡

ሌላው በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረበው የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ድግግሞሽ ስለ ቃል ክፍል ሲሆን በምዕራፍ ሰባት ገፅ 128 ቃላቱን በዐ.ነገር ውስጥ በትክክለኛ ቦታቸው ተጠቅማችሁ አሳዩ፡፡ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመተራራም ዐ.ነገሮቻቸውን

አሻሽለው እንዲገልፁ ተደርጓል፡፡ ምሳሌ፡- ነገረኛ ቅፅል፣ ነገረኛ ሰው አይግጠማችሁ፡፡... በዚሁ ምዕራፍ በተመሳሳይ ገጽ በትዕዛዝ ሁለት ላይ በቅንፍ ውስጥ ያሉትን ግሶች በምሳሌው መሠረት ለክፍት ቦታዎች በሚስማማ መልክ በመቀየር ዐ.ነገሮችን እንዲያሟሉ ያዝዛል፡፡ ምሳሌ፡- ህፃኑ ልጅ ልብሱን በእናቱ (አጠበ)፡፡ መልስ አሳጠበ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በተለጣጣቂነት ምዕራፍ ዘጠኝ ገጽ "155" ዐረፍተ ነገሮችን በመስጠት ያሉትን የስምና የግስ ሙያዎች ለይታችሁ በመተንተን አሳዩ፡፡ ምሳሌ፡- ሜላት የቤቱን ወለል አጠበች፡፡ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ስም የሆኑ ቃሎች ሜላትና የቤት ወለል ናቸው፡፡ ስለዚህም የአረፍተ ነገሩ ባለቤት-ሜላት፣ ተሳቢ-የቤቱ ወለል፣ ማሰሪያ አንቀጽ-አጠበች ይሆናል በሚል ቀርቧል፡፡

የአረፍተ ነገር ክፍሎችን በሚመለከት በምዕራፍ አምስት በገጽ "86" የአረፍተ ነገር ክፍሎች በሚል አጭር ማብራሪያ በማስፈር በተገለፀው ምሳሌ መሠረት ባለቤት፣ ተሳቢና ማሠሪያ አንቀፆች አውጥተው በሰንጠረዥ እንዲያሳዩ ያዝዛል፡፡ በተመሳሳይ ምዕራፍ ስምንት ገፅ "142" ላይ "አረፍተ ነገር" በሚል ርዕሥ ምንባብ የቀረበ ሲሆን ምሳሌዎችን በመስጠት በቀጣይ ገፅ የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች በስማዊ ሀረግና በግሳዊ ሀረግ ክፍለው እንዲያቀርቡ ያዝዛል፡፡ ለአብነት፡- ትናንት የመጣችው ተማሪ በኢትዮጵያ የትምህርት ቤቶች መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ከፍተኛ ውጤት አመጣች፡፡ ሌላው የሀረግ አጥነቶችን በተመለከተ የቀረበ ሰዋስው ሲሆን በምዕራፍ አራት ገጽ "71" ስለ ሀረጋት አመሠራረት ማብራሪያ ከሰጠ በኋላ በምሳሌ ስማዊ ሀረግ፣ ቅፅላዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ በሚል አብራርቶ በገፅ "72" ትዕዛዝ አንድ የተለያዩ የሐረግ አብነቶች ቀርበው በየትኛው የሀረግ ዓይነት እንደሚመደቡ እንዲገልፁ ያዝዛል፡፡ ምሳሌ፡- ሶፊ ብርድ ልብስ አለው፣ ዘገየ በጣም ታታሪ ሰው ነው፣...በተመሳሳይ በምዕራፍ ስምንት ገፅ 141 በትዕዛዝ አንድ ቃላትን በመምረጥ ስማዊ ሐረጎችን መስርቶ ከዚያም አረፍተ ነገር እንዲሰሩባቸው ያዝዛል፡፡ **ምሳሌ**፡- ረዥም ገመድ፣ የእግር መንገድ፣ የፈተና ወረቀት...

ከላይ በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ የቀረበውን የሰዋስው ትምህርት መልመጃ አደረጃጀት ተለጣጣቂነት አንፃር ስናይ ተገቢ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያው ተግባር የቃል ክፍሉን የሀረግ አይነቱን እንዲለዩ ማድረጉ፣ ከዚህም ተነስተው የመሰረቱት ሀረግ በመጠቀም አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱና እንዲለዩ መደረጉ የመልመጃው ድግግሞሽ ከቀላል ወደ ከባድ ተገቢ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሌሎች ለሁለት ጊዜ ተደጋግመው የቀረቡና ለአንድ ጊዜ የቀረቡ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች አደረጃጀታቸው ከተለጣጣቂነት አንፃር ከተማሪዎች የቀደመ እውቀት በመነሳት የተደራጁ በመሆናቸው ተገቢ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፡- በ9ኛ ክፍል

የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ምዕራፍ አራት ገፅ “175” የቃላት መጥበቅና መላላት መልመጃ ተሰጥቷል። በዚሁ ምዕራፍ ገፅ “67” የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ማብራሪያ ከነመልመጃው ቀርቧል። ስለዚህ በዚህ ክፍል ሳይደገሙ መቅረባቸው በተማሪዎች ላይ አይረሴነትና ትውስታን ከመፍጠር አንፃር ተገቢነት የለውም።

ከዚህ ጠቅለል አድርገን የምንረዳው የተገኘው መረጃ ከተለጣጣቂነት አንፃር በርካታ የሰዋስው ትምህርታዊ መልመጃዎች እንደሚገኙ ሲሆን በአንፃሩ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የሰዋስው ትምህርት መልመጃ አደረጃጀት ከተለጣጣቂነት አንፃር ውስን ክፍተቶች እንዳለበት ከሰነድ ፍተሸው የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

**ሠንጠረዥ ”ነ” የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሰዋስዋዊ መልመጃዎች ድግግሞሽ የሚያሳይ ሠንጠረዥ**

በአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች ከተለጣጣቂነት አንጻር በአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከተለጣጣቂነት አንፃር የቀረቡ መልመጃዎችን በቁጥር የተገኙትን ወደ ፐርሰንት በመቀየር ከዚህ በታች በቀረበው ሠንጠረዥ ለማየት ተችሏል።

| **በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች** | **የድግግሞሽ መጠን** | | |
|---|---|---|---|
| | **ገፅ** | **በቁጥር** | **በ%** |
| ነፃና ጥገኛ ምዕላድ | 14፣82፣83፣125 | 4 | 17.5 |
| የተለያዩ የሀረግ ዓይነቶችን መመስረትና አይነታቸውን በመናገር ሀረጎችን ተጠቅሞ አረፍተ ነገር መመስረት | 26፣27፣72፣113 | 4 | 17.5 |
| አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃት /ሀረጋት | 43 | 1 | 4.3 |
| የአረፍተ ነገር አይነቶችን ለዩ | 44፣72፣138 | 3 | 13 |
| የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች | 45 | 1 | 4.3 |
| ከግስ ስምንና ቅፅልን መመስረት | 60፣61፣86፣139 | 4 | 17.5 |
| የአረፍተ ነገር ስልቶች | 61፣114፣124 | 3 | 13 |
| በቃላት ውስጥ ሚጠብቁና ሚላሉ ድምፆች | 84 | 1 | 4.3 |
| የቃላት አውዳዊ ፍች | 85 | 1 | 4.3 |
| የቃላት ቀጥተኛ ፍች | 96 | 1 | 4.3 |
| **ድምር** | **23** | **23** | **100** |

ሠንጠረዥ "ነ" የሚያመለክተው በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ መልመጃዎች ለምን ያህል ጊዜ ተደጋግመው እንደቀረቡ ነው፡፡ ድግግሞሹ ሶስት መልመጃዎች ማለትም ነፃና ጥገኛ ምዕላድ፣ የሀረግ አይነቶችና አመሠራረት ከግስ ስምና ቅፅል መመስረት የሚሉት እያንዳንዳቸው ለአራት ጊዜ (17.5%) የተደጋገሙ ሲሆን የአረፍተ ነገር ስልቶችና የአረፍተ ነገር አይነቶች እያንዳንዳቸው ለሶስት ጊዜ (13%)፣ የቃላት አውዳዊ ፍቺ፣ ቀጥተኛ ፍቺ፣ የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ፣ አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት/ሀረጋት፣ በቃል ውስጥ የሚጠብቁና የሚላሉ፣ (የሚረዝሙና የሚያጥሩ) ድምፆች እያንዳንዳቸው ለአንድ ጊዜ (4.3%) ብቻ ቀርበዋል፡፡ ከቀረቡት አስር የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ንዑስ ርዕሶች ውስጥ አምስቱ ከሶስት እስከ አራት ጊዜ በድግግሞሽ የቀረቡ ሲሆን ሌሎቹ አምስት መልመጃዎች ደግሞ ለአንድ ጊዜ ብቻ ቀርበዋል፡፡ 28.5% ያህል የመልመጃ ድግግሞሽ እንዳለም መረዳት ይቻላል፡፡ ሆኖም በሰዋስው መልመጃዎች መካከል የተመጣጠነ የመልመጃ ድግግሞሽ እንደ ሌለ መረዳት ይቻላል፡፡

ከመልመጃ ድግግሞሽ መረጃ በመነሳት የነፃና የጥገኛ ምዕላድን መልመጃ ከተለጣቂነት ስናይ በምዕራፍ አንድ ገፅ "14" አስር ቃላት ተሰጥቶ የመጀመሪያውን ምሳሌ በመሥራት በምሳሌው መሠረት ቀሪዎቹን ዘጠኝ ቃላት በውስጣቸው ያለውን ነፃና ጥገኛ ምዕላድ በመለየት ተንትነው እንዲያሳዩ ያደርጋል፡፡ በምዕራፍ 6 ገፅ "82" ትዕዛዝ አንድ ላይ ደግሞ ስድስት ቃላት ተሰጥቶ አንዱ ምሳሌ ሲሆን አምስቱ ቃላት ከትዕዛዝ አንድ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ነፃና ጥገኛ ምዕላዱን ለይተው የጥገኛ ምዕላዱን አገልግሎት እንዲገልፁ ያዝዛል፡፡

በምዕራፍ ዘጠኝ ገፅ "125" ሁለት ምሳሌዎችን አስቀድሞ በመስጠት ስምንት ነፃ ምዕላድ (ቃላት) እና አሥር ጥገኛ ምዕላድ በመስጠት ለነፃ ምዕላዱ ከጥገኛ ምዕላዱ የሚስማማቸውን በመቀጠል ቃላትን እንዲመሠርቱ ያዝዛል፡፡

ለአብነት፡- ጥገኛ ምዕላድ -ኣት፣ -ኢያ፣ -ማ...ነፃ ምዕላድ መጥረግ፣ ግብ፣ ጦስ፣...ተሰጥተዋል፡፡

የመልመጃ አደረጃጀት ክትትሎሹን ከላይ በቀረበው ማብራሪያ የምንረዳው በመጀመሪያው ምዕራፍ ገፅ "14" ላይ የቀረበው በምዕራፍ ስድስት ገፅ "82" እና "83" ከቀረበው ጋር ያለው ተለጣጣቂነት ተገቢ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያው ተግባር ከተሰጡት ቃላት ውስጥ ነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን ተንትነው የጥገኛ ምዕላዱን ተግባር እንዲገልፁ ማድረጉ መልመጃው ደረጃ በደረጃ እያደገና ከቀላል ወደ ከባድ ተከታትሎ የተደራጀ መሆኑን ያሳያል፡፡

በገፅ “125” በምዕራፍ ዘጠኝ ስለ ምዕላድ የቀረበው መልመጃ ደግሞ ከመልመጃ ቅለትና ክብደት አንፃር በምዕራፍ አንድ ገፅ “14” እና በምዕራፍ ስድስት በገፅ “82” እና “83” ስለምዕላድ ከቀረበው መልመጃ ጋር ሲነፃፀር ቀላል ነው፡፡ ምክንያቱም በመልመጃ ደረጃ ከነፃና ጥገኛ ምዕላድ ይልቅ ቃላት ከፍ ያለ ደረጃ አላቸው፡፡ ስለዚህ በመጀመሪያው መስጠት ያለበት ተግባር ነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን ለያይቶ በመስጠት ቃላትን እንዲመሠርቱ ማድረግና ከዚያም ከተመሠረቱት ቃላት ነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን በመተንተን የጥገኛ ምዕላዶችን አገልግሎት እንዲገልፁ ቢደረግ ድግግሞሹም ሆነ ከቀላል ወደ ከባድ የመደራጀቱ ሂደት የተሳካ ይሆናል፡፡ በመፅሀፍ ተደራጅተው የቀረቡት የነፃና የጥገኛ ምዕላድ አደረጃጀትም በመጀመሪያ መቅረብ ያለበት በመጨረሻ የቀረበ በመሆኑ አደረጃጀቱ ከተለጣጣቂነት አንፃር ክፍተት ያለበት መሆኑን ያመለክታል፡፡

ሌላው በፅሑፍ ውስጥ የቀረበው የሰዋስው ትምህርት መልመጃ ድግግሞሽ ሀረግ ሲሆን በምዕራፍ ሁለት ገፅ “26” በአምስቱ የቃል ክፍል አማካኝነት የተለያዩ ሀረጎች ተመስርተው ምሳሌ ከተሰጠ በኋላ በተመሳሳይ ከአምስቱ የቃል ክፍል አምስት ቃላት ተሰጥቶ የቃል ክፍሉን፣ ሀረግ በመመሥረት የሀረግ አይነቱን እንዲገልፁ ተደርጓል፡፡

ምሳሌ፡- ነቀፌ፣ ገበሬ፣…በዚሁ ምዕራፍ ገጽ “27” ትዕዛዝ ሁለት ቀደም ብለው በገፅ “26” በመሰረታቸው ሀረጎች አንዳንድ አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያዝዛል፡፡ በዚህ ገፅ ስለ ሀረግ ምንነትና አይነት አጠር ያለ ማብራሪያ በመስጠት በትዕዛዝ ሶስት አንድ ምሳሌና አስር አረፍተ ነገሮች ተሰጥተው በአረፍተ ነገሩ ውስጥ የተሰመረባቸውን ሀረጎች መሪ ቃልና አይነት እንዲያመለክቱ ተደርጓል፡፡

<u>ምሳሌ</u>፡- “ሁሉም ሰው እንደ ንብ ታታሪ ሠራተኛ መሆን አለበት፡፡”

ከዚህ በመቀጠል ምዕራፍ አምስት ገጽ “72” ላይ “ምንም የማይቻል ነገር የለም” በሚል ርዕሥ ከቀረበው ፅሑፍ ውስጥ የሚገኙ ሀረጋትን በአምስቱ የሀረግ ዓይነት እንዲመድቡ ያዝዛል፡፡ በምዕራፍ ስምንት ገፅ “113” ስለ ሀረጋት አመሰራረት ገፅ “114” ትዕዛዝ አንድ የተለያዩ የሀረግ አይነቶች ቀርበው በተሰጠው ባዶ በታለካ የሀረጉ ስያሜ እንዲገልፁ ያዝዛል፡፡ ምሳሌ፡- እንደ ወንድሙ ክፉኛ፣ ከእኛ ቤት ጎን፣…

ከላይ የቀረበው ሰዋስው ትምህርት መልመጃ አደረጃጀት ከተለጣጣቂነት አንፃር ስናይ ተገቢ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያው ተግባር የቃል ክፍሉንና የሀረግ አይነቱን እንዲለዩ

ማደረጉ፣ ከዚም ተነስተው የመሰረቱትን ሀረግ በመጠቀም አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱና በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ደግሞ የተመሰረተባቸውን የሀረግ አይነቶች እንዲለዩ መደረጉ ከዚያም ከፅሑፍ ውስጥ ሀተጋት በማውጣት በአይነት እንዲመድቡ መደረጉ፣ የመልመጃዎቹ ክትትሎሽ ከቀላል ወደ ከባድ ማለትም ከቃል ተነስቶ በአረፍተ ነገርና ከአረፍተ ነገር በላይ በሆነ ሰፋ ባለ ፅሑፍ ውስጥ የሚገኙ ሀረጋትን እስከ መለየት ድረስ የቀረበ መሆኑ ተገቢ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከግስ ስምና ቅፅልን መመስረት የሚለው ሰዋስዋዊ መልመጃ ለአራት ጊዜ ያህል ተደጋግሞ ቀርቧል፡፡ ምዕራፍ አራት ገፅ “60” ላይ ከአንድ ግስ እስከ አምስት የሚደርሱ (ጥሬ ዘራዊ፣ ሳቢ ዘራዊ፣ አርእስታዊ፣ ግልጋሎታዊና ውጤታዊ) ስሞችን መመስረት እንደሚቻል በምሳሌ በማሳየት በኤ ደ፣ ለበሰ፣ … የሚሉ አምስት ቃላትን በመስጠት ከላይ የተዘረዘሩትን ውልድ ስሞች እንዲመሰርቱ ያደርጋል፡፡

በተመሳሳይ ገፅ “601 ላይ ከግስ ቅፅል መመስረት እንደሚቻልና አንዳንድ ግሶች ግን ቅፅላዊ እርባታ ሌላቸው መሆኑን አጠር ያለ ገለፃ ከነምሳሌው በመስጠት ገፅ “61” ባከነ፣ አሸን፣ ተለቀ፣ … የሚሉ ሰባት ግሶችን በመስጠት ቅፅል እንዲመሠርቱ ጠያዝዛል፡፡ በዚሁ ገፅ ትዕዛዝ ሰባት “ለ” ሶስት ምሳሌዎችንና በላ፣ ካሳ፣ … የሚሉ አራት ግሶችን በመስጠት ውልድ ቅፅል እንዲመሠርቱ ያደርጋል፡፡ ምዕራፍ አስር ገፅ “139” ትዕዛዝ ሶስት ሁለት ምሳሌዎችንና በላ፣ ዓሳ፣… የሚሉ ስድስት ግሶችን በመስጠት ስም መሰል ቃልና ቅፅል እንዲመሰርቱ ያዝዛል፡፡

ይህንን ከመረጃ ቅለትና ክብደት አንጻር የተሰጡት የቃላት ድግግሞሽ ተገቢ እንዳልሆኑ ከዚህ በፊት ለማሳየት ተሞክሮአል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ከተከታታይነት አንፃርም የቀረበው መረጃ ድግግሞሽ ተገቢ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም መልመጃው ለተማሪዎች አዲስና የቀደመ እውቀታቸውን ያገናዘበ ባለመሆኑ ማብራሪያ ሚያስፈልግ ቢሆንም ማብራሪያ አልተሰጠውም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከቀላል ወደ ከባድ ደረጃ በደረጃ መልመጃው የቀረበበት ሁኔታ አይታይም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በመልመጃነት የተሰጡ ቃላት አላስፈላጊ ድግግሞሽ ይታይባቸዋል፡፡ ምሳሌ ገፅ “61” “በዛ” የሚለው ቃል (ግስ) ገፅ “86” ሰከረ፣ በላና ካለ የሚሉ ቃላት በዚሁ መልመጃ በድጋሚ ገፅ “139” የቃላት ለውጥ ሳይኖር በተመሳሳይ ተግባርና መልመጃ ቀርቧል፡፡ ይህ ደግሞ እያደገ መምጣቱን ሳይሆን ባለበት እንዲቀጥልና ቀድመው የተሰሩት ደጋግመው እንዲሰሩት መደረጉ አሰልቺ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ በዚህ መልመጃ ያለው ተከታታይነት ተገቢ እንዳልሆነ ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መፅሐፍ ውስጥ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች አደረጃጀትና አቀራረብ ከተለጣጣቂነት አንፃር የተወሰነ ውስንነት ያላቸው ቢሆንም በአብዛኛው ተገቢ እንዳልሆኑ ከሰነድ ፍተሻው ከተገኘው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳኑ ከተገለፀው የምሁራን ሀሳብ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡

ከዚህ ጠቅለል አድርገን የምንረዳው በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀትና አቀራረብ ከተለጣጣቂነት አንፃር ውስን ክፍተት እንዳለበት ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ በጥቅሉ በአንድ መጽሐፍ ከመልመጃ ተለጣቂነት አንፃር ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው ውስን ክፍተት እንዳለበት ሲሳይ ድግግሞሽን አስመልክቶ መረዳት ሚቻለው የተገኘው መረጃ ከሌሎች የሰዋስው መልመጃዎች ጋር ያልተመጣጠነ ድግግሞሽና ውስን ክፍተቶች ያሉበት መሆኑን ነው፡፡

### 4.1.2.3 የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀት ከውህደት አንፃር

የተማሪዎችን ግንዛቤ ለማስፋት ታሳቢ በማድረግ የአማርኛ ቋንቋ መፅሐፍ ውስጥ ሰዋስው ትምህርት መልመጃ በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ለውን የመልመጃ ጎናዊ ዝምድና የሚመለከት ውህደታዊ አደረጃጀት ነው፡፡ የዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ ካለው የእንግሊዝኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከተደራጁ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ጋር ያላቸው ዝምድና ምን እንደሚመስል ሰነዱን ዋቢ በማድረግ ከዚህ በታች ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

በዘጠነኛና ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ምዕራፍ ሁለት ገፅ “86” በገፅ “26” ሰዋስው በሚል ንዑስ ምዕራፍ የአረፍተ ነገር ክፍሎችን እንዲለዩ ያዝዛል፡፡ በተመሳሳይ በዘጠነኛ ክፍል የእንግሊዝኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ደግሞ ምዕራፍ Grammar and Usage በሚል ንዑስ ስር Chose the one that best completes each sentence በማለት አረፍተ ነገሩን በባለቤትና በማሰሪያ አንቀፅ እንዲሞሉ ያዝዛል፡፡

ከአረፍተ ነገር ምሣሬታና ዋና ዋና ክፍሎች ስንወጣ በተመሳሳይ ደረጃ በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ምዕራፍ ሁለት ገፅ “27” በገፅ “27” በመሠረቱት ሀረግ አማካኝነት አረፍተ ነገር እንዲመሠርቱ ያዝዛል፡፡ በ10ኛ ክፍል የእንግሊዝኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ደግሞ ምዕራፍ “Complete the sentences below using the verb of time” በማለት አረፍተ

ነገሩን ተውሳከ ግሳዊ ሀረጉን ተጠቅመው እንዲያሟሉ ያደርጋል። ይህ ደግሞ በሁለቱም መፅሀፍ ሀረግን ተጠቅመው አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያስተምራል።

ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ በአስረኛ ክፍል እንግሊዝኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ቃላት ላይ ቅጥያን የሚያመለክቱ በገፅ "101" (suffix) ላይ ለምሳሌ Berele is the fastest and strongest athlete in Ethiopia በሚል ከቀረበ በኋላ መልመጃ እንዲሰሩ ያዝዛል። ሌላው መስተዋድድን (Preposition) በገጽ 104 በምሳሌነት I want home and did my my homework በሚል ቀርቦ ሌሎችን ተማሪዎች በጋራ እንዲሰሯቸው ያዝዛል፤ ስምና ግስን በተመለከተ ደግሞ በገጽ 9 ላይ ከነማብራሪው ቀርቧል። The verb to be ex

I am in this group, you eye in the group` He/she/we/they… በጥቅሉ እነዚህና ሌሎች የሰዋስው መልመጃዎች ተካተው ይገኛሉ።

በተመሳሳይ በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ስለ ቅጥያ ሀረጋትን የተመለከተ፣ ስለ አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት እንዲሁም የቃላት ክፍሎችን የሚመከቱ ማብራሪያዎች እና መልመጃዎች በገፅ 82 ምዕላድን የተመለከቱ፣ 27 ስምን ተመለከቱ፣ 43 አያያዥ ቃላትን በተለያዩ ምዕራፎች ቀርበዋል።

ከላይ በተጠቀሰው መሠረት እንግሊዝኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍን ለአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍትጎናዊ ግንኙነት አንጻር የሰዋስው መልመጃዎች ምን ያህል ተመጋጋቢ እንደሆኑ ማየት ይቻላል። የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች የቃላት ቅጥያዎች፣ አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት እንዲሁም ስምና ግስን የተመለከቱ መኖራቸው ውህድነት ያላቸው መሆኑን ያመለክታል። የመማሪያ መፃህፍቱን ከውህድነት አንፃር ሲመዘን በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች ተደራጅቷል ለማለት አያስደፍርም። ከላይ የቀረቡትን ማሳያዎች በማንሳት በአብዛኛው በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች የአማርኛና እንግሊዝኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተደራጁት የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ጎናዊ ግንኙነት እንዳላቸው ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

### 4.1.3 የመማሪያ መጻህፍቱ ከመርሀ ትምህርቶቹ ጋር ያላቸው ዝምድና

ከላይ በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸው መማሪያ መጽሐፍትና መርሃ ትምህርት ጥብቅ ትስስር እንዳላቸው ተገልጿል። ከዚህም አኳያ የዘጠነኛና አስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ

መፅሐፍ ከመርሃ ትምህርቶቹ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ከዚህ በታች በተናጠል ለማየት ተሞክሯል፡፡

**ሠንጠረዥ "ኘ" የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርትና መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች**

| **የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች** | **በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ የቀረቡ** | **በአስረኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ የቀረቡ** | **በዘጠነኛና በአስረኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ የቀረቡ** |
|---|---|---|---|
| ነፃ ምዕላድ፣ ጥገኛ ምዕላድ | አለ | አለ | አለ |
| ሀረግ፣ የሀረግ ዓይነት | አለ | አለ | አለ |
| የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች | አለ | አለ | አለ |
| አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት | አለ | አለ | አለ |
| የአረፍተ ነገር ክፍሎች፣ አይነቶች | አለ | አለ | አለ |
| የሀረግ አመሰራረት ተራና ውስብስብ አረፍተ ነገር | አለ | አለ | አለ |
| መነሻና መድረሻ ቅጥያዎች፣ የቃል ክፍሎች፣ የቃላት ፍች፣ የቃል ክፍሎች ሙያዎች | አለ | አለ | አለ |
| የቃላት መላላትና መጥበቅ አገባባዊ ፍች | አለ | አለ | አለ |

ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው የዘጠነኛ እና አሥረኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ያካተታቸው የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች በሙሉ ለሁለቱም ደረጃዎች በተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ አብዛኛዎቹ እየተደገሙ ጥቂቶቹም ሳይደገሙ ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህ አንጻር መማሪያ መጻህፍቱ እና መርሀ ትምህርቱ ጥብቅ ትስስር እንዳላቸው ማየት ተችሏል፡፡ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች በሙሉ በመርሃ ትምህርቱ ዝግጅቱም ውስጥ ተካተው ይገኛሉ፡፡ በዚህ መሠረት የዘጠነኛ እና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍቱና የተዘጋጁት መርሃ ትምህርቶች ስምምነት ያላቸው ናቸው ለማለት ያስደፍራል፡፡

## 4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2009 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስተር ታትመው በሥራ ላይ በዋሉት በዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት የሰዋስው ትምህርት መልመጃ አቀራረብና አደረጃጀት መፈተሽ ሲሆን በውስጡ ሶስት ንዑሳን አላማዎችን ይዟል፡፡ የእነዚህን ዓላማዎች እውነት ለማረጋገጥ በሠነድ ፍተሻ ከመማሪያ መፅሐፍቱ የጥናቱ አስፈላጊ የሆነን መረጃ በመሰብሰብ በጥናቱ የመረጃ ትንተና ላይ በዝርዝር ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

የዚህ ጥናት የመጀመሪያው ንዑስ ዓላማ በዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ያላቸውን አቀራረብ መፈተሽ የሚል ነው፡፡ በመሆኑም በዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው መልመጃዎች የቋንቋውን ሥርዓት ፍቺና አገልግሎት አቀናጅቶ ከማቅረብ አንፃር፣ ከተማሪ ተኮር አቀራረብ፣ ከሂደት ተኮር እና ከእውናዊነት አንፃር የሚሰጡት ትኩረት ዝቅተኛ እንደሆነ በመረጃ ትንተና ላይ ተረጋግጧል፡፡

የዚህ ጥናት ውጤትም በተስፋዬ (1993) የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ለቋንቋው ስርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት ትኩረት ያልሰጡ ናቸው ከሚለው ውጤት ጋር ይዛመዳል፡፡ ሌላው ከሰላም (2010) በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የአቀራረብ ክፍተት እንዳለባቸውና ለተግባቦቱ ትኩረት እንዳልሰጡ ከሚለው የውጤት ግኝት ጋር ይመሳሰላል፡፡

በተመሳሳይ የዚህ ጥናት ውጤት ሰሚራ (2010) ከሚለው ጥናታዊ ፅሑፍ ውስጥ ለሂደት ተኮር አቀራረብ ተመጣጣኝ የሆነ ትኩረት እንዳልተሰጣቸው ከሚለው የውጤት ግኝት ጋር ይዛመዳል፡፡ ከዚህ አኳያ በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ከአቀራረብ አንፃር ለመገምገም የሚያስችሉ መስፈርቶች ተግባራዊ ስልት ትወራን መሠረት አድርጎ የሚዘጋጅ የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ለቋንቋው አገልግሎት ወይም ፍቺ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች የቋንቋውን አገልግሎታዊ ትግበራን መሠረት በማድረግ ይቀርባሉ፡፡ እውናዊነትን መሠረት ባደረጉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ላይ ያተኩራሉ፡፡ እንዲሁም በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት የሚቀርቡት ሰዋስዋዊ መልመጃዎች ወይም ተግባራት የተማሪዎችን የእርስ በርስ ግንኙነትን የሚያጠነክሩ ተማሪዎች ያላቸውን ሀሳብ የሚለዋወጡበት ስሜታቸውን ለጓደኞቻቸው የሚገልፁበት፣ ተማሪዎች በቡድንና በጥንድ

በመሆን በሚያከናውኗቸውና የተማሪዎችን የመተማመን፣ የማደራጀትና መግለጽ ብቃታቸውን የሚያጎለብቱ መሆን እንደሚገባቸው የሚገልጹትን ምሁራን (Harmar 1991) ሀሳብ ያላገናዘበ መሆኑን ያሳያል።

ሌላው የዚህ ጥናት ንዑስ ዓላማ በመማሪያ መፅሐፍቱ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀታቸው ምን እንደሚመስል መመርመር የሚል ነበር። የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀት ከተከታታይነት አንፃር የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ከዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ አንፃር ሲታይ በውስጡ ያካተቷቸው መልመጃዎች ሰፊና ተከታታይነት ባለው መልኩ የተደራጀ ቢሆንም መልመጃዎችን በቀደመው ክፍል ዝቅተኛ እንደሆኑ ተለይቷል።

በተመሳሳይ ከተለጣጣቂነት አንፃር ሲታዩ በተወሰነ መልኩ ደረጃቸውን ጠብቀው የተደራጁ ቢሆንም በተወሰነ መልኩ ደግሞ የመልመጃ ድግግሞሽ ላይ ችግር እንደሚስተዋል ተለይቷል። በመጨረሻም ከውህደት አንፃር ሲታዩ በሚፈለገው መልኩ ተደራጅተው የቀረቡ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል። የዚህ ጥናት ውጤትም ከሰሚራ (2010) እና ሰላም (2010) የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ይዘቶች ሲደራጁ ሰፊና ተከታታይነት ባለው መልኩ የተደራጁ ቢሆንም አላስፈላጊ የይዘት ድግግሞሽ ላይ ችግር ያለባቸው የውጤት ግኝት ጋር ይመሳሰላል።

በዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ከተከታታይ፣ ከተለጣጣቂነትና ከውህደት አንፃር ተደራጅተው መቅረብ እንዳለባቸው የሚገልፁን ምሁራን (ተስፋዬ1981)፣(Tyler 1949) ሀሳብ ያላገናዘበ መሆኑን ያሳያል።

የዚህ ጥናት ሶስተኛው ዓላማ የዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት መፈተሽ የሚል ነበር። ተተኳሪ በሆኑት መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች በሙሉ ከመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ተካተው የተገኙና መርሃ ትምህርቱና መማሪ መፅሐፍቱ ተጣጥመው የቀረቡ ናቸው። ይህንን ሀሳብ የሚደግፉ ምሁራን መማሪያ መጻሕፍት ማለት መርሃ ትምህርቱን መሠረት በማድረግ የሚቀረፅና ከቋንቋ ትምህርት አንጻር ሲታይ በውስጡ ተማሪዎችን ተግባቦት ብቃት ሊያለብቱ የሚችሉ የተለያዩ የዕውቀትና የክህሎት ዘርፍ የትምህርት ይዘቶችን ሥርዓታዊ በሆነ መንገድ በማደራጀት አካቶ

የሚይዝ ሠነድ ሲሆን አብዛኛዎቹ መምህራን መርሃ ትምህርት ማለት መማሪያ መጻሕፍት ማለት ነው ብለው ስለሚያስቡ መማሪያ መጻሕፍት ማለት በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የተገለፁትንና ተጨባጭ የሆኑ ገፅታዎች የሚቀርቡበት መሣሪያ ነው (Nunan 1989)። ሀሳብ ያላገናዘበ መሆኑን ያሳያል።

በአጠቃላይ ከላይ የተገለፁት የውጤት ማብራሪያ ላይ የታዩ ችግሮች እንዳይደገሙ ሊሠራ እንደሚገባ የሚያመለክት ነው።

# ምዕራፍ አምስት፡- ሰማጠቃለያ እና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

በምዕራፍ አንድ ላይ እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2004 ዓ/ም ተሻሽለው በወጡት የዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል አጠቃላይ የሆነ ግምገማ ማካሄድ ነው፡፡ ይህ አቢይ ዓላማ የሚያካትታቸው ዝርዝር ዓላማዎች፡-

- በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አቀራረብ መፈተሽ፣
- በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀታቸው ምን እንደሚመስል ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት ተተኳሪ በሆኑት መጻሕፍት በተደረገው የሠነድ ፍተሻ የሚከተሉት ውጤቶች ሊገኙ ችለዋል፡፡

ከአቀራረብ አንፃር በመማሪያ መፅሐፍቱ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች ሲታዩ እንደሚከተለው ይገለፃሉ፡፡

የሰዋስው መልመጃዎችን አቀራረብ ስንመለከት

- ✓ የቋንቋውን ሥርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት አቀናጅተው ማያቀርቡ ስለሆነ ለተማሪዎች የተለያዩ መዋቅሮችን እንዴት፣ የትና መቼ መጠቀም እዳለባቸውና በዲስኩር ጊዜ የትኛው የሰዋስው መዋቅር መቅደምና መከተል እንዳለበት የማያሳውቁ፣
- ✓ ተማሪዎች በጥንድና በቡድን በመሆን እንዲወያዩ ወይም የተለያዩ የሰዋስው መልመጃዎችን እንዲሠሩ፣ ሀሳባቸውን የማያደርጉና የተማሪዎች ትብብራዊ መማርና ተግባቦታዊ ብቃት የማያጎለብቱ፣
- ✓ እውናዊነትን ያልተላበሱ ስለሆነ ተማሪዎች በቋንቋው የመግባባት ክህሎታቸውን በእውኑ ዓለም ላይ ያለውን አጠቃቀም በክፍል ውስጥ የበለጠ እንዲጠቀሙበት የማያስችሉ፣
- ✓ ከምሳሌው ተነስተው ወደ ህጉ የማይሄዱ በመሆኑ ተማሪዎች የቋንቋውን ሥርዓት ለይተው እንዲያውቁ ከማድረግ ውጪ ታላሚውን ቋንቋ በመጠቀም በእውኑ ዓለም ላይ

በትክክል እንዲግባቡበት የማያደርጉ መሆናቸውን በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ከተደረገው የሠነድ ፍተሻ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከአደረጃጀት አንፃር በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡት ሰዋስው መልመጃዎች ሲታዩ እንሚከተለው ይገለፃሉ፡፡

መማሪያ መፃህፍቱ ከተከታታይነት አንፃር ሲታይ የተወሰኑ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎችን መሠረት በማድረግ እንደተዘጋጁ ለመለየት የተቻለ ሲሆንና ከቀጣይነት አንፃር የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ከዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሐፍ አንፃር ሲታይ በውስጡ ያካተታቸው መልመጃዎች ሰፊና ተከታታይነት ባለው መልኩ የተደራጀበት ሁኔታ ያለ ቢሆንም መልመጃዎችን በቀደመው ክፍል ከማካተት አኳያ በዘጠነኛ ክፍል ያሉት ዝቅተኛ እንደሆኑ ተለይቷል፡፡

መማሪያ መፃህፍቱ ከተለጣጣቂነት አንፃር ሲታይ የተወሰኑ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ያሉት የሰዋስው መልመጃዎች በተወሰነ መልኩ አደረጃጀታቸውን ጠብቀው የተደራጁ ቢሆንም፤ በተወሰነ መልኩ ደግሞ የመልመጃ ድግግሞሽ ላይ ችግር እንደሚስተዋል ተለይቷል፡፡

በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አብዛኛዎቹ ድግግሞሽ የሚታይባቸው ሲሆን አንድ ጊዜ ተከስተው የማይቀጥሉም እንዳሉ ማወቅ ተችሏል፡፡ ከተለጣጣቂነት አንፃር የቀረበው መልመጃ ድግግሞሽ ተገቢ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም መልመጃ ለተማሪዎች አዲስና የቀደመ ዕውቀታቸውን ያገናዘበ ባለመሆኑ ማብራሪያ የሚያስፈልግ ቢሆንም ማብራሪያ አልተሰጣቸውም፡፡

መማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ከውህደት አንፃር ሲታዩ በሚፈለገው መልኩ ተደራጅተው የቀረቡ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች በሙሉ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ተካተው የተገኙና መርሃ ትምህርቱና መማሪያ መጻህፍቱ ተጣጥመው የቀረቡ ናቸው፡፡

## 5.2 አስተያየት

ከላይ ከቀረበው ማጠቃለያ ሀሳብ መሠረት ከዚህ በታች የቀረቡት ነጥቦች በጥናቱ የተስተዋሉ ግኝቶችን ለማሻሻል በመፍትሔ ሀሳብነት የቀረቡ ናቸው፡፡

- በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች በቋንቋው ሥርዓት ላይ ብቻ ተንተርሰው የሚቀርቡ ከሆነ የተማሪውን ተግባቦታዊ ችሎታ ሊያጎለብቱ ስለማይችሉ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ብቃት ለማጎልበት በቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው መልመጃዎች የቋንቋውን ሥርዓት፣ ፍቺና አገልግሎት በተጣጣመ ወይም በተቀናጀ መልኩ የሚያስተምሩ ቢሆኑ፣
- እውናዊነትን ያልተላበሱ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎችን በመጠቀም የቋንቋ ትምህርትን የምናስተምር ከሆነ ተማሪዎች በቋንቋው የመግባባት ክህሎታቸውን በእውኑ ዓለም ላይ ያለውን አጠቃቀም በክፍል ውስጥ የበለጠ እንዲጠቀሙበት ለማድረግ በቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው መልመጃዎች እውናዊነትን ተላብሰው ቢቀርቡ፣
- ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ዝቅተኛ የሆነ የሆነ ትኩረት የሚሰጡ የሰዋስው መልመጃዎች የተማሪዎችን የእርስ በርስ ግንኙነት የሚያጠነክሩ፣ የመተንተን፣ ማደራጀት፣ የመግለፅ ብቃታቸውንና የመማር ፍላጎታቸውን እንዲሁም ትብብራዊ መማርንና ተግባቦታዊ ብቃታቸውን የማያዳብሩ፣ ያለቸውን ሃሳብ እንዲለዋወጡና ስሜታቸውን ለጓደኞቻቸው እንዲገልፁ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን የእርስ በርስ ግንኙነት ለማጠናከር፣ መተንተን፣ የማደራጀት፣ የመግለፅ ብቃታቸውንና የመማር ፍላጎታቸውን እንዲሁም ትብብራዊ መማርንና ተግባቦታዊ ብቃታቸውን ለማዳበር በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው መልመጃዎች ለተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት ቢሰጡ፣
- ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ መሠረት በማድረግ ያልተዘጋጁ የሰዋስው መልመጃዎች ከህጉ ተነስተው ወደ ምሳሌው የሚሄዱ ስለሆነ ለተማሪዎች ነፃነትን የማይሰጡ፣ ትምህርቱን በንቃት እንዲማሩ የማያደርጉና የችግር ፈቺነት ክህሎታቸውን የማያዳብሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም ለተማሪዎች ነፃነት ለመስጠት፣ ትምህርቱን በንቃት እንዲማሩ ለማድረግ እንዲሁም የችግር ፈቺነት ክህሎታቸውንለማጎልበት በቋንቋ

መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የሚቀርቡ የሰዋስው መልመጃዎች ከምሳሌው ተነስቶ ወደ ህጉ ወይም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚቀርቡ ቢሆኑ፣

- በመማሪያ መጻህፍት ከቀጣይነት አንፃር የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ከዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ አንፃር ሲታይ በውስጡ ያካተታቸው መልመጃዎች ሰፊና ቀጣይነት ባለው መልኩ የተደራጁበት ሁኔታ የተሻለ ሆኖ በዘጠነኛ ክፍል ያሉ መልመጃዎች ከአሥረኛ ክፍል ጋር ከማጣጣም አኳያ የሰዋስው መልመጃዎች መልመጃዎች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ መቅረብ ቢችሉ፣
- በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ያሉ አንዳንድ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ተለጣጣቂነት ባለው መልኩ ለማደራጀት፣ በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው መልመጃዎች ጥቅል በሆነ እና ከተማሪዎች የቀደመ ዕውቀት ጋር በተመጣጠነ መልኩ ለማቅረብ እንዲቻል በየምዕራፎቹ ውስጥ የሰዋስው መልመጃዎች የሚደራጁበት ሁኔታ ቢመቻች፣
- በዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አብዛኛዎቹ ድግግሞሽ የሚታይባቸው ሲሆን አንድ ጊዜ ተከስተው የማይቀጥሉ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች የአደረጃጀታቸውን ቅደም ተከተል በመጠበቅ የተማሪዎችን ግንዛቤ ታሳቢ አድርገው መቅረብ ቢችሉ፣
- አጠቃላይ በሆነው የመማሪያ መጻህፍቱ ዝግጅት በሥርዓት የተደራጀና ቅደም ተከተል የጠበቀ ከቀላል ወደ ከባድ የሚሄድ፣ ከጎንዮሽ ውህደነት በአግባቡ የተደራጀ በመሆኑ ቀጣይ በሚዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ላይም ይህ ሁኔታ ቢደገም።

# ዋቢፅሑፎች


ማረው አለሙ፡፡ (2003)፡፡ *ዘመናዊ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች፡፡* (2ኛ እትም)፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ ማተሚያ ቤት፡፡

ሰላም ታዬ፡፡ (2010)፡፡ በ2004 በተዘጋጀው የ10ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አመራረጥና አደረጃጀት ከሥነ-ትምህርታዊ ሰዋስው አንፃር የተዘጋጀ ጥናት፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

ሰሚራ አሊ፡፡ (2010)፡፡ በደቡብ ክልል በ2009 ዓ/ም ሥራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተካተቱ የስዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

ባዬ ይማም፡፡ (2002)፡፡ *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡*፡ (3ኛ እትም)፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡

ተስፋዬ ሸዋዬ፡፡ (1981)፡፡ ስነልሳንና ቋንቋን ማስተማር፡፡ አዲስ አበባ፤ (ያልታተመ)፡፡

ተስፋዬ በቀለ፡፡ (1981)፡፡ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ለ8ኛ ክፍል አማርኛ ኢ-አፈ-ፈት ተማሪዎች በተዘሣጀው የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና ግምገማ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2004)፡፡ *የምርምር መሠረታዊ መርሆችና አተገባበር*፡፡ አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት

Brown, H.D. (1994). *Principle of Language Learning and Teaching* (3rd ed.).New Jersey Prentice Hall Regents.

Cooper, M. (1995). *Cooperative Learning an Approachfor Large Enrollment Courses*, Journal of Chemical Education Vol 72, No. 2, P162-164

Cunnings Worth, A. (1995) *Choosing your course book*. London: MacMillan. Heinemann.

Ellis, R. (1997), *SLA Research and Language Teaching*. Oxford: Oxford University Press.

Harmer, J. (1991).*The Practice of English Language Teaching* (2nd Ed.)London Longman.

Krashen, (1983).*Second Language Acquisition*. Mexico: Cup.

Nunan, D. (1989). *Designing Task for Communicative Classroom* Cambridge.Cambridge University Press.

Richards, J., and Rodgers, T. (2001).*Approaches and Methods in Language Teaching* (2nd Ed). New York: Cambridge. Cambridge University Press.

Tarone, E. and Yule, G. (1989).*Focus On The Language Learning* Oxford. Oxford University Press.

Tyler, J. (1949). *Basic Principles of Curriculum and Instruction*. Chicago: Chicago University Press.

# አባሪዎች

## ዲላ ዩኒቨርሲቲ ማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች) ሥነ-ፅሑፍ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

### ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

የዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ተገቢነትን ለመገምገም ለሰነድ ፍተሻው የቀረቡ መስፈርቶች ከተለያዩ ምሁራን ተሰባስበው የተወሰዱ ሲሆን መስፈርቶቹ Harmer (1991) Brown (1994) Nunan (1989) የመማሪያ መፅሐፍ ግምገማ ለማድረግ አስቀድሞ መለኪያ ሊሆኑ እንደሚገባ ያስቀመጧቸው መለኪያዎች ናቸው፡፡ (በCunning Worth) እና ተስፋዬ ሸዋዬ በዝርዝር ያስቀመጧቸውን የሰዋስው መልመጃዎች አደረጃጀት መስፈርቶች ተጠቅሜያለሁ፡፡

የዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍት ሰዋስዋዊ መልመጃዎች አቀራረብ

1. የቋንቋውን ሥርዓት ፍቺና አገልግሎት አቀናጅቶ ከማቅረብ አንጻር
2. የተማሪ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚሰጡ
3. በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብን መሠረት በማድረግ የቀረቡ መሆናቸውን ተፈትሸዋል፡፡

የዘጠነኛና አሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍት ሰዋስዋዊ መልመጃዎች አደረጃት፡-

1. ከተከታታይነት አንፃር
2. ከተለጣጣቂነት አንፃር
3. ከውህደት አንፃር እንዴት እንደተደራጁ መልመጃዎች ተፈትሸዋል፡፡